ሀይድ (የወር አበባ ደም)

ኢስቲሀዷ (የበሽታ ደም)

ኒፋስ (የወሊድ ደም)

ጥንቅር፡- አህመድ ሲራጅ ሙሀመድ

24 - ሸዋል -1441

መግቢያ

باسم الله الرحمن الرحيم

الحمد لله الذي علم بالقلم، علم الإنسان مالم يعلم، والصلاة والسلام على من بعث معلما للناس وهاديا وبشيرا، وعلى أله وصحبه ومن تبعهم بإحسان إلى يوم الدين

وبعد:-

ንጽህና የእምነታችን ግማሽ ነው። ለስራዎቻችን ተቀባይነትም አንደኛው ቅድመ ሁኔታ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ ሙስሊም ስለንጽህና የመማር ግዴታ አለበት። ጌታችንም ንጽህና ጋር በተያያዘ የደነገጋቸው የተለያዩ ህግጋቶች አሉ። ከነዚያ ድንጋጌዎች ዉስጥ ከፊሎቹ ሴቶችን ብቻ ይመለከታሉ፡፡ እነሱም ሀይድ፣ ኢስቲሀዷ እና ኒፋስ ናቸው፡፡ እነዚህን ድንጋጌዎች በትክክል ለመተግበር ሲባል ሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥተው ሊማሯቸው ይገባል። ወንዶችም ቢሆኑ ሴት ልጆቻቸውን፣ ባለቤቶቻቸውን፣ እህቶቻቸውን ከዚያም አልፎ መላውን ሙስሊም ማህበረሰብ በጥልቀት ያስተምሩ ዘንድ ይሄን የእውቀት መስክ በተገቢው መልኩ መማር ይጠበቅባቸዋል። ባሎች ሚስቶቻቸውን፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ስለ እነዚህ ጉዳዮች ማስተማር ከተሳናቸው ከአስተማሪዎች ዘንድ ሄደው እንድማሩ ሊፈቅዱላቸው ይገባል፡፡ ስለ እነዚህ ርእሶች መማራቸው ግዴታ ስለሆነ ባሎችም ይሁኑ ወላጆች ባይፈቅዱም ሴቶች ይሄን ክልከላ በመተው ከመሻይኾችና

ከአስተማሪዎች ዘንድ ሄደው የመማር ግዴታ አለባቸው። ምክንያቱም ስለ ሀይድ በጥንቃቄ መማር ካልቻሉ ሶላታቸው፣ ጾማቸው፣ ሀጃቸው፣ ቁርአታቸው፣ ትዳራቸው በጥቅሉ በጣም በርካታ አምልኳዊና ማህበራዊ መስኮች ይናጉባቸዋል። ጉዳዩ የዚህን ያክል አሳሳቢ መሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት፣ በዚህ ዘርፍ ላይ የተጠናቀሩ ጽሁፎች አለመኖራቸውን ታሳቢ በማድረግ እንድሁም የበርካታ ሴቶች የእለት ከእለት ጥያቄዎች መሆናቸውንም በመገንዘብ የተወሰኑ ምሁራኖችን ኪታቦች እንደማጣቀሻነት በመጠቀም ይችን አጭር፣ ግልጽና በምሳሌ የተደገፈች ማስታወሻ አዘጋጅቻለሁ። በጽሁፌ ዉስጥ በጠቀስኳቸው ነጥቦችና የተሻሉ ናቸው ብዬ በመረጥኳቸው አቋሞች ዙሪያ መረጃዎችን መጥቀስ ያስፈልጋል ብዬ ባመንኩባቸው ቦታዎች ላይ ጥቂት መረጃዎችን አስቀምጫለሁ። የማስታወሻዋ ይዘት በጣም ሰፊና አሰልቺ እንዳይሆን በመስጋት የመረጃዎቹን ትርጓሜ እና የተሻለ ብዬ ከመረጥኩት ሀሳብ ጋር በቀጥታ የሚዛመደው የቁርአኑ አንቀጽ ወይም የሀዲሱ ክፍል የትኛው እንደሆነም ከመግለጽ ተቆጥቤያለሁ። ይች ማስታወሻ ለጀማሪዎችና ሰፋፊ መጽሀፍቶችን ለማያነቡ ወንድምና እህቶች የተዘጋጀች በመሆኗ በእያንዳንዱ ባነሳሁት ነጥብ ዙሪያ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚፈልግ ማንኛውም ሙስሊም በርእሱ ዙሪያ በሰፊው የተዘጋጁ መጽሀፍቶችን እንዲያነብ እጠቁመዋለሁ። ጉዳዩ የፊቅህ ጉዳይ በመሆኑ በእያንዳንዱ ነጥብ ዙሪያ በርካታ የልዩነት ሀሳቦች ያሉ

መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ማናችንም ብንሆን ከእከሌ ሸይኽ ወይም ከዚህ መዝሀብ ዉጭ ያለን ማንንም ቢሆን አልቀበልም ከሚል ጭፍን ተከታይነት እና ጰያፍ ወገንተኝነት ተላቀን ከመረጃዎቹ አሳማኝነት አንጻር የተሻለ ሆኖ የተገኘውን አቋም የመከተል ግዴታ እንዳለብን ለማስታወስም እወዳለሁ፡፡ በዚች ማስታወሻ ዉስጥ የተሻለ ብዬ የመረጥኩት ሙሉ በሙሉ ዉድቅ (ባጢል) ወይም ፍጹም አርአያ የሌለው አቋም ሆኖ ከተገኘ እርማት ይሰጡኝም ዘንድ በትህትና ጠይቃለሁ፡፡

ይህ ትንሽ የሆነ ጥረት የአላህ ዉዴታ ብቻ የተፈለገበት፣ ተቀባይነትን ያገኘ፣ በዱንያም በአኺራም የሚጠቅም፣ የብዙዎችን ችግር የሚፈታና ለተሻለ ስራ የሚያበረታታ ይሆን ዘንድ ጌታዬን እማጸነዋለሁ፡፡

إنْ أُرِيدُ إلاَّ الإِصْلاَحَ مَا اسْتَطَعْتُ وَمَا تَوْفِيقِي إلاَّ بِاللهِّ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَإِلَيْهِ أُنِيب { هود -٨٨

ለአስተያየትዎ nahmed.siraj@gmail.com *ወይም*

http://t.me/Nasir_Ah *ይጠቀሙ፡፡*

አህመድ ሲራጅ ሙሀመድ

የሀይድ ትርጉምና ተያያዥ መልእክቶች

1. ሀይድ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ብያኔዎችና ህግጋቶች በትክክል መገንዘብ ከየትኛውም የፊቅህ አርዕስት የበለጠ ፈታኝና ዉስብስብ በመሆኑ ምክንያት ታላላቆች ሳይቀሩ በዚህ ርእስ ዙሪያ እንደተሳሳቱበት ኢማሙ ነወዊይ መጅሙዕ ላይ አስፍረዋል፡፡ ይሄም የራሱ የሆኑ ምክንያቶች አሉት። ከእነዚያም ዉስጥ ሀይድ እና ኢስቲሀዷ ሴቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በመሆናቸው በዘርፉ ላይ የሚጽፉትም ይሁን የሚናገሩት ምሁራኖች አጋጥሟቸው የማያውቅን ጉዳይ ስለሆነ የሚጽፉት ችግሩን በትክክለኛ ገጽታው አለመረዳታቸው፣ የተለያዩ ኢኢማዎች የሚያስቀምጧቸው መርሆዎች አይደለም ለሌሎች አንባቢዎችና ለሴቶች ለራሳቸው ለአዘጋጆቹ ሳይቀር በጣም ዉስብስብ መሆናቸው፣ በተለያዩ ጊዜያት ሴቶች የሚጠቀሟቸው መድሀኒቶች የሀይድን ሁኔታ ማዘበራረቁ፣ ከመረጃዎች ይልቅ በግለሰቦች እይታ ላይ የተንጠለጠሉ አቋሞችና አስተያየቶች መንሰራፋታቸው፣ ታማኝና ብቃት ያላቸው ሙስሊም የህክምና ባለሙያዎች በሀይድ ዙሪያ ወጥና አሳማኝ የሆኑ መረጃዎችን በመጽሀፍ መልኩ ማዘጋጀት አለመቻላቸው ተጠቃሾች ናቸው።

2. ሀይድ በቋንቋ ደረጃ ፈሳሽ ማለት ሲሆን ሸሪኣዊ የሆነው ትርጓሜው ደግሞ በታወቀ የጊዜ ገደብ ዉስጥ አቅመ ሄዋን ከደረሰች ሴት ማህጸን የሚለቀቅና በመራቢያ አካል በኩል የሚፈስ፣ ምንም አይነት የህመም፣ የቁስለት፣ የዉርጃና የዉልደት መንስኤ የሌለው ተፈጥሯዊ ደም ነው። በዚህ ገለጻ መሰረት አንድት ሴት የሚያጋጥማት አንዷት ወይም ሁለት ተብሎ የሚቆጠር የደም ጠብታ የሀይድ ደም ተደርጎ አይወሰድም። ምናልባት በከባድ ሸክም፣ በህመም ወይም በመጨናነቅ ምክንያት የተፈጠረ ሊሆን ይችላል። የሀይድ ትርጓሜም የዚህን አይነት ደም አካታች አይደለም።

◆ عن علي رضي الله عنه قال: إذا رأت المرأة بعد ما تطهر من الحيض مثل غسالة اللحم أو القطرة من الرعاف أو فوق ذلك أو دون ذلك، فلتنضح بالماء ولتصل ولا تغتسل، إلا أن ترى دماً غليظاً، فإنما هي ركضة من الشيطان في الرحم. رواه ابن ابي شيبة

3. ሀይድ በአረብኛ አስር አካባቢ ተጨማሪ መጠሪያ ስሞች አሉት። ከፊሎቹ መጠሪያ ስሞች በሀዲስም ተረጋግጠዋል። ከእነዚያም ዉስጥ ኒፋስ፣ ጦምስ፣ ዶሂክ፣ ሙሰለሳህ፣ ኢዕሷር፣ ኢክባር፣ ዲራስ፣ ዒራክ እና ፊራክ ይገኙበታል።

4. ሀይድ ከሰው ልጆችም ዉጭ ባሉ ከፊል እንስሳቶች ላይ እንደሚከሰት ከፊል ምሁራኖች በኪታቦቻቸው ላይ አስፍረዋል። ዐለማዊ ምሁራኖችም ይሄንኑ ሀሳብ ያጠናክሩታል።

5. ሀይድ በሁሉም የሴት ልጆች ላይ አላህ ያጸናው ጉዳይ ነው።

◆ عن عائشة رضي الله عنها قالت: دخل علي الرسول وانا ابكي قال مالك ؟ انفست ؟ قلت نعم, قال إن هذا امر قد كتبه الله على بنات آدم . رواه مسلم

6. ለመጀመሪያ ጊዜ ሀይድ ያጋጠማት ሴት እናታችን ሐዋእ ነች። ክስተቱም አባታችን አደም እና እሷ ጀነት ዉስጥ በፈጸሙት ሀጢያት ምክንያት በቅጣት መውጣታቸውን ተከትሎ ነው።የኢብኑ ዐባስ رضي الله عنهما ንግግርም ከላይ የተጠቀሰውብ ሀዲስ ያጠናክራል።

◆ عن ابن عباس: ان ابتداء الحيض كان على حواء بعد ان أهبطت من الجنة. رواه الحاكم وابن منذر

7. የሀይድ ደም መኖር የጤናማነትና ማርገዝ የመቻል ምልክት ሲሆን፣ መዛባቱ ወይም ሙሉ በሙሉ አለመኖሩ ደግሞ የጤና መታወክን ጠቋሚ ነው። የሀይድ ሙሉ በሙሉ አለመኖር ማርገዝ አለመቻልን ይጠቁማል።

8. የሀይድ ደም ሴት ልጅ ለአቅመ ሄዋን (ቡሉግ) መድረሷን ጥቋሚ ተደርጎ ይወሰዳል። ይሄንን ተከትሎም ማንኛውም

አይነት ሸሪዓዊ ድንጋጌዎች ሁሉ ይመለከቷታል። ይህ በሁሉም ዑለማኦች ዘንድ ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ ነው።

- عن عائشة رضي الله عنها قالت : قال النبي صلى الله عليه وسلم : لاتقبل صلاة حائض إلا بخمار. رواه أحمد
- قال ابن حجر: أجمع العلماء على ان الحيض بلوغ في حق النساء. فتح الباري ٥/٥٦٠

9. የሀይድ ደም ተፈጥሯዊ በመሆኑ ምክንያት የሴቶች ተፈጥሯዊ የአካል አወቃቀር፣ የአካባቢያቸው የአየር ንብረት ሁኔታ እንድሁም የቤተሰባቸው የዘረመል ተጽእኖ ስለሚያሳድርባቸው በተለያዩ ሁኔታ ይከሰታል። ይህም ማለት በሀይድ ምክንያት ከፊሎች ከባድ የህመም ስሜት ሲፈጠርባቸው ከፊሎቹ ዘንድ የሚፈጥረው የህመም ስሜት ደግሞ አነስተኛ ይሆናል። ከፊሎቹ በጣም በጥቂት ቀናት ወይም ሰአታት ሲነጹ ቀሪዎቹ ደግሞ ሳምንታቶችን ሊወስድባቸው ይችላል።

የሀይድ ደም መለያዎች

1) የሀይድ ደም ቀድሞ ማህጸን ግድግዳ ላይ በጠጣርነት ተከማችቶ የነበረ ደም ነው። ስለዚህ ወደ ዉጭ ከፈሰሰ በሁላ ለሁለተኛ ጊዜ የጠጣርነት (የመድረቅ) ባህሪ የለውም።

2) የሀይድ ደም በዋነኝነት ወፍራም እንጅ ቀጭን ፈሳሽ አይደለም።

3) ቀለሙ በዋነኝነት ጥቁር ወይም ወደ ጥቁር ያመዘነ እንጅ ንጹህ ቀይ ወይም ቡኒ አይደለም።

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لفاطيمة بنت ابي حبيش : إذا كان دم الحيض فإنه أسود يعرف ... رواه ابو داود (يعرف : بضم الياء وفتح الراء)

4) የሀይድ ደም በተለያዩ ምክንያቶች ሴቶችን ከሚያጋጥማቸው የደም ፍሰት በተለዬ መልኩ መጥፎ ጠረን አለው።

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لفاطيمة بنت ابي حبيش : إذا كان دم الحيض فإنه أسود يعرف....رواه ابو داود (يعرف : بضم الياء وكسرة الراء)

5) የሀይድ ደም በሚፈስበት ጊዜ የሞቃትነት ስሜት ይፈጥራል።

ሀይድና እድሜ

1) የሀይድ ደም መነሻና መቋጫ የእድሜ ገደብ እንዳለው የሚጠቁሙ መረጃዎች ሁሉ ወይ ደካማ ናቸው ወይም ግልጽነት የጎደላቸው ናቸው። ስለዚህ ሀይድ ከ7 ወይም 9 ወይም 12 አመት እስከ 50 ወይም 60 አመት ድረስ ባለው የእድሜ ክልል ብቻ ነው የሚከሰተው የሚያስበል የቁርአንም የሀዲስም እንድሁም ትክክለኛ የሰለፎችም መረጃ የለም። የሴቷ ልጅ የኑሮና አስተዳደግ ሁኔታ፣ የምትኖርበት አካባቢ የአየር ንብረት ምንነት እንድሁም የዘር ሀረጎቿ የዘረመል ተጽእኖ በልጃገረዷ የሀይድ መነሻና መቋጫ እድሜ ላይ የጎላ ተጽእኖ አላቸው። ያልተለመደ ከመሆኑ ጋር ከፊሎች ከዘጠኝ አመት ቀድመው ሀይድ ሊያዩ ይችላሉ። ምናልባትም ከሃምሳ አመት በላይ እድሜ ያላቸው ሴቶችም ሀይድ ሊያጋጥማቸው ይችላሉ። አላህም የሀይድን ጉዳይ ሲገልጽ ከደሙ መኖር አለመኖር ጋር አያያዘው እንጅ ከእድሜ ጋር አላቆራኘውም። ስለዚህ የሴት ልጅ እድሜዋ ምንም ይሁን ምን የሚታወቅ መንስኤ የሌለው ፈሳሽ ደም እስካጋጠማት ድረስ የሀይድ ደም ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ የበርካታ ምሁራኖች አቋም ነው። ከእነዚህም ዉስጥ ኢማሙ ማሊክ፣ ኢብኑ ሙንዚር፣ ኢብኑ ተይሚያህ፣ ኢብኑል ቀይም፣ ሸውካኒ፣ አልባኒ፣ ሰዕዲ፣ ዑሰይሚኒና ኢብኑ ባዝ ተጠቃሾች ናቸው።

10. ማንኛዋም ህጻን ከመሆኗ የተነሳ ወይም በማርጀቷ ምክንያት ማርገዝ የማትችል መሆኗ የታወቀ ሴት የሚያጋጥማት የደም ፍሰት ፍጹም የሀይድ ደም ሊሆን አይችልም። የዚህ አይነት ደም በበሽታ ደም ነው የሚወሰደው።

- قال إمام مالك : فأما الطفلة الصغيرة فما رأت من الدم حكم له بأنه دم علة وفساد لإنتفاء الحيض مع الصغر. المدونات الكبرى مع مقدمة ابن الرشد
- وقال ايضا : فأما العجوز التي لا تشبه ان تحيض فما رأت من الدم حكم له بأنه دم علة وفساد لإنتفاء الحيض مع الكبر كما ينتفي مع الصغر . المدونات الكبرى مع مقدمة ابن الرشد

11. እድሜዋ ከሀምሳ ይለፍም አይለፍም የአንድት ሴት ሀይድ ለአመታት ካቆመ በኋላ መልሶ የሀይድን ደም መለያዎች የሚታዩበት የደም ፍሰት ቢያጋጥማት ያ ደም በሀይድ ደም ነው የሚታሰበው፡፡ ለረጅም ጊዜ ከተቋረጠ በኋላ ስለተከሰተ በሀይድ አይወሰድም የሚያስብል ምንም አይነት መረጃ የለም፡፡ ደሙ እስከተገኘ ድረስ ሀይድ ተደርጎ መወሰድ እንዳለበት ቁርአኑም ሀዲሱም ይጠቁማል፡፡ ይህ የከፊል ማሊኪያዎች፣ የኢብኑ ሀዝም እና የኢብኑ ተይሚያህ አቋም ነው፡፡

◆ عَنْ عَائِشَة رضي الله تعالى عنها قالَتْ: قال النَّبيُّ ﷺ: إذَا أقبَلَتِ الحَيْضَةُ، فَدَعِي الصَّلاَة، وإذَا أدْبَرَتْ، فاغْسِلِي عَنْكِ الدَّمَ، وصلِّي. روه النسائي وصححه الألباني في إرواء الغليل

ሀይድና የጊዜ ቆይታው

12. በሰፊው የሚታወቀውና በብዛትም የተለመደው የሀይድ ደም ፍሰት የቆይታ ጊዜ ስድስት ወይም ሰባት ቀናት ቢሆንም ቁርጥ ያለ ዝቅተኛና ከፍተኛ የመቆያ ጊዜ ገደብ ግን የለውም። ለከፊሎች ከአንድ ቀን ያነሰን ያክል የጊዜ ቆይታ ሊኖረው ይችላል። ለሌሎች ደግሞ ከአስራ አምስት ቀናት በላይ ሊቆይባቸው ይችላል። ስለዚህ የሀይድን ትንሹን የጊዜ ገደብ አንድ ቀን ከነሌሊቱ እንድሁም ከበዛ አስራ አምስት ቀን በሚል ገደብ ማስቀመጥ አላህ በግልጽ ባላስቀመጠው ጉዳይ ላይ በዘፈቀደ እንደመናገር ነው የሚቆጠረው። አላህም በቁርአኑ የጠቀሰው እስከሚጸዱ ድረስ አትቅረቧቸው በሚል እንጅ ለዚህን ያክል ቀን አትቅረቧቸው በሚል አይደለም። የቁርአኑ አይነት መልእክት ያላቸው በርካታ ሃዲሶችም አሉ። ከነዚያም ዉስጥ

◆ عَنْ عَائِشَة رضي الله تعالى عنها قالَتْ: قال النَّبيُّ ﷺ: إذَا أقبَلَتِ الحَيْضَةُ، فَدَعِي الصَّلاَة، وإذَا أدْبَرَتْ، فاغْسِلِي عَنْكِ الدَّمَ، وصلِّي. روه النسائي وصححه الألباني في إرواء الغليل

ይሄን በተመለከተ ሸይኽ ዑሰይሚኒ አላህ ይዘንላቸውና ከሴቶች ዉስጥ ፍጹም ሀይድ የማያዩ እንዳሉት ሁሉ ለሰአታቶች ብቻ የሚቆይ ሀይድ የሚያጋጥማቸውም አሉ ይላሉ። ስለዚህ ፈሳሹ ደም ከሀይድ የሚለየው ነገር ሳይኖር እስከቀጠለ ድረስ የሀይድ ደም ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ የበርካታ ዑለማኦችና አኢማዎች አቋም ነው። ከእነዚህም ዉስጥ ኢማሙ ማሊክ፣ ኢብኑ ሙንዚር፣ ኢብኑ ተይሚያህ፣ ኢብኑል ቀይም፣ ሸውካኒ፣ አልባኒ፣ ዑሰይሚኒና ኢብኑ ባዝ ተጠቃሾች ናቸው። ይህ ከመረጃዎችም ጥንካሬ አንጻር ተወዳዳሪ የሌለውና የተሻለው አቋም ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ መታወቅ ያለበት ቁልፍ ነጥብ የሀይድ ደም በየትኛውም መልኩ ቢሆን ለአንድ ወር ሙሉ አይቀጥልም።

13. በዚህ ዘመን ሴቶች በሚጠቀሟቸው የተለያዩ የወር አበባ ማዘግያ እና ማፍጠኛ ወይም የወሊድ መቆጣጠሪያ መድሀኒቶች ምክንያት በየወሩ አብዛኛውን ቀናት የሚሸፍን የደም ፍሰት የሚኖርባቸው ሴቶች በጣም በርካታዎች ናቸው። ታዲያ ይሄን ወቅታዊዉንና ብዙ ሴቶችን የሚፈታተን የብዙዎች ጉዳይ በተመለከተ ከፊል የዘመናችን ዑለማኦች ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ያለውን የደም ፍሰት በበሽታ ደም ልታስበው ይገባል የሚል እይታ አላቸው። ምክንያታቸውን ሲያስረዱ ይህ ሁኔታ እጅግ በጣም በርካታ ሴቶችን የሚያጋጥም መሆኑ፣ በየወሩ ሀያ ምናምን ቀናቶችን በሀይድ የምታሳልፍ ሴት

የእድሜዋን አብዛኛውን ጊዜ ያለ ሶላትና ጾም አሳለፈች ማለት መሆኑ፣ ይህን ያክል ጊዜን በሀይድ መቁጠር ትዳር ላይ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ እጅግ በጣም የጎላ ስለሆነ ከባድ ማህባራዊ ቀውስ የሚያስከትል መሆኑ እነዚህ ጉዳዮች ደግሞ ከሸሪዓው መሰረታዊ መርህ ጋር መጣጣም የማይችሉ ናቸው የሚል ነው። ከዚህ ዉጭ መረጃ ብለው የሚያቀርቧቸው የመከራከሪያ ሀሳቦች ግን ትክክለኝነትና ግልጽነት የጎደላቸው ናቸው። በዘመናችን ሸይኽ ሰዒድ ኸስላን አላህ ይጠብቃቸውና መጀመሪያ ላይ ሀይድ ገደብ የለውም የሚል አቋም ነበራቸው። ኋላ ላይ ግን አቋማቸውን አሻሽለው ሀይድ ከአስራ አምስት ቀን እንደማያልፍ ይገልጻሉ። ሸይኽ ዑሰይሚኒም አንድ ቀን አልፎ አንድ እያለ ወሩን ሙሉ የሚቀጥል ወይም ከወሩ ዉስጥ ንጹህ የምትሆንበት ጊዜ በጣም አናሳ ከሆነ ከ15 ቀን በኋላ ያለውን የደም ፍሰት በበሽታ ደም መቁጠሩ የተሻለ እንደሆነ ይገልጻሉ። በሸርሁል ሙምቲዕም ላይ መጀመሪያ ላይ ሀይድ ገደብ እንደሌለው አስፍረው ኋላ ላይ ግን ከ15 ቀን በላይ ያለውን ጊዜ ከሀይድ አለመቁጠሩ የተሻለ እንደሆነ ይጠቅሳሉ። የህክምና ባለሙያዎችም ቢሆኑ ሀይድ ቢበዛ እስከ 15 ቀን ድረስ ነው የሚዘገየው ይላሉ። ይህ የሻፊዒዮች፣ የማሊኪዮች እና የሀንበሊዮች በጥቅሉ የአብዛኛዎቹ ምሁራኖች አቋም ነው። ሸይኽ ኢብኑ ባዝም ይሄንኑ ይደግፋሉ።

◆ قال النووي رحمه الله "ثبت مستفيضا عن السلف من التابعين فمن بعدهم أن أكثر الحيض خمسة عشر يوما، وأنهم وجدوه كذالك عيانا، ... منهم عطاء، والحسن، وعبيد الله بن عمر، ويحيى بن سعيد، وربيعة، وشريك، والحسن بن صالح، وبن مهدي، رحمهم الله"

14. ምንም እንኳ ያልተለመደ ክስተት ቢሆንም አንድት ሴት በአንድ ወር ዉስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ሀይድ ሊያጋጥማት ይችላል፡፡ ስለዚህ በሁለት የሀይድ ጊዜያቶች መካከል የሚኖረው የንጽህና ቀናት ይሄን ያክል ነው ማለት አይቻልም ማለት ነው፡፡ ይሄን ሀሳብ የሚደግፍ ክስተትም በዐሊይ رضي الله عنه ዘመን ተፈጥሯል። በመሆኑም በአንድ ወር ዉስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ሀይድ ማየቷን በመግለጽ የምትከራከር ሴት (ለምሳሌ የፍቺ ዒዳን ስለማጠናቀቋ) መከራከሪያዋ ተቀባይነት ያገኘላት ዘንድ ሀሳቧን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ ግድ ይላታል፡፡ በጥቅሉ በተለመደው የወር አበባ ኡደት ላይ ተመስርታ የምትከራከር ሴት የመከራከሪያ ሃሳቧን የሚያረጋግጥ መረጃ እንድታቀርብ አትገደድም፡፡

15. ጥቅል በሆነ መልኩ እርጉዝ ሴት የሀይድ ደም አያጋጥማትም፡፡

◆ قال إمام أحمد " إنما تعرف النساء الحمل بانقطاع الدم" المغني 1/٤٤٤

ይህ የቁርአንም፣ የሀድስም እንድሁም የህክምና ባለሙያዎችም ጥቆማ ነው፡፡ የሀነፊያዎች፣ የሀንበሊያዎችና

ቀዳሚው የሻፊዒይ፣ የኢብኑ ሙንዚር፣ የኢብኑ ሀዝም እንድሁም በዘመናችን የአልባኒ፣ የሳዑዲ ቋሚ የፈታዋ ኮሚቴ አቋም ነው።

◆ عن عائشة رضي الله عنها قالت : إن الحبلى لا تحيض فإذا رأت الدم فالتغتسل والتصل. روه الدارمي وصححه الألباني في إرواء الغليل

16. እርጉዝ ሴት የፍቺንም ይሁን የባለቤቷን የሞት ዒ'ዳ የምትቆጥረው በመውለጃ ቀኗ ብቻና ብቻ ስለሆነ በእርግዝናዋ ወቅት ሀይድ ቢያጋጥማት ይህ ሀይድ ፍጹም ዒዳን ለመቁጠር አያገለግልም። በተጨማሪም ይህ ሀይድ ትዳር ለመመስረት የሚያስችልም አይደለም። ምክንያቱም እርጉዝ ሴት ማግባት የምትችለው ልጅ ከወለደች በኋላ ብቻ ነው።

◆ قال الله عز وجل : "{ وأولات الأحمال أجلهن ان يضعن حملهن} الطلاق -٤

17. አንድት ሴት የተለመደው ሀይዷ ስንት ቀን እንደሆነ ታውቅ ዘንድ የመጀመሪያዎቿን ሶስት የሀይድ ጊዜያቶች መከታተል አለባት የሚሉ ምሁራኖች አሉ። ምሳሌ፦ በመጀመሪያዎቹ ሶስት ጊዜያቶች የሀይድ ደም ፍሰቱ የቆየው ወሩ በገባ በመጀመሪያው ሳምንት ለ5 ተከታታይ ቀናት ከሆነ የተለመደው የሀይድ ጊዜዋን በእያንዳንዱ ወር መጀመሪያ ሳምንት ላይ ለአምስት ቀን እንደሚቀጥል አድርጋ ታስበዋለች። ይህን

ማወቅ ለምን አስፈለገ ከተባለ ደሙ ለረጅም ጊዜያት የሚቆይ ከሆነ የሀይድ ቀናቶቿን በግምት ከምትወስደው ይልቅ በዚህ ልምድ መሰረት ማስላቷ ተገቢ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ ለተከታታይ 40 ቀን ደም ቢፈሳት ከነዚህ ቀናቶች ዉስጥ ወር በገባ የመጀመሪያ ሳምንት ላይ ያሉትን 5ቱን ቀናት የሀይድ ጊዜ ብላ በመውሰድ ቀሪውን ጊዜ በበሽታ ደም ታስበዋለች። ነገር ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ሀይድ ያየች ልጅ ከሁለተኛው ወር ጀምሮ የደም ፍሰቱ ኢስቲሀዷ ሆኖ ረጂም ጊዜን ቢቀጥልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋጠማትን የሀይድ ቆይታ እንድ ልምድ ተጠቅማ ትጾዳለች።

18. ለመጀመሪያ ጊዜ የደም ፍሰት ያጋጠማትን ልጅ ሀይድ ላይሆን ይችላል በሚል ለጥንቃቄ ሲባል እንድትጾም እና ሶላት እንድትሰግድ ማዘዝ፣ ቁርአንን በእጇቿ ይዛ እንዳታነብ ማገድ እንድሁም ከግንኙነት እንድትቆጠብ ማድረግ፣ ምናልባት ሀይድ ቢሆንስ በሚል እሳቦት ደም እየፈሰሳት የጾመችውን ጾም ኋላ ደሙ ሲያቆም ቀዷእ እንድታወጣ መደንገግ ምንም አይነት መረጃ የሌለው የመዝሀብ ምርጫ ከመሆኑም ባሻገር ግልጽ የሆኑ ሀዲሶችንና የዑለማኦችን ስምምነትም መጻረር ነው። ስለዚህ ምንም አይነት የታወቀ መንስኤ የሌለው ደም እስካጋጠማት ድረስ ሀይድ ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት።

ልምድን ያልጠበቀ ሀይድ

19. የሀይድ ጊዜዋ ከተለመደው የጊዜ ቆይታ የተወሰነ ቀን ከጨመረና እሷም የሀይድን ደም ከኢስቲሀዷ ደም መለየት የምትችል ከሆነ (በቀለሙ፣ በጠረኑ ወይም በሌላ መሰል መለያ መንገድ ተጠቅማ የኢስቲሀዷ መሆኑን ካረጋገጠች) የሀይድን ጡሀር ትታጠብና ከዚያ በኋላ የሚፈሰውን ደም ኢስቲሀዷ ትወስደዋለች። ነገር ግን የሀይድን ደም ከኢስቲሀዷ ደም መለየት ከተሳነት የጊዜ ቆይታው ከተለመደው ጊዜ የተወሰነ ቀን ቢጨምርም ቢቀንስም ከሀይድነቱ አይወገድም። ሀይድ በደሙ መኖር አለመኖር እንጅ በታወቀው ልምድ ላይ የተገደበ ነው የሚል ምንም አይነት መረጃ የለም።

20. የተለመደው የሀይድ ጊዜዋ ወር በገባ በመጀመሪያው አካባቢ ቢሆንና ይህን ልምድ ባልጠበቀ መልኩ በሌላ ወቅት (በወሩ አጋማሽ ወይም መጨረሻ ላይ) ቢያጋጥማት የተለመደውን ጊዜ ስላልጠበቀ ሀይድ አይደለም ተብሎ አይወሰድም። ልምድ ያላት ሴት ያጋጠማት የደም ፍሰት ከተለመደው ቀን ይብዛም ይነስም፣ ከተለመደው ወቅት ይቅደምም ይዘግይም የሀይድ ደም ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ የሻፊዒዮች መዝሀብ ነው። ሸይኹል ኢስላም ቢን ተይሚያህና ኢብኑ ዑሰይሚኒም ይሄንኑ

አቋም ይመርጣሉ። ከዚህ ተቃራኒ ሃሳብ ያላቸው ምሁራኖች ሀሳባቸውን የሚደግፍ አሳማኝ መረጃ የላቸውም።

21. አንዷት የታወቀ የሀይድ ኡደት ያላት ሴት በታወቀው የጊዜ ገደብ ዉስጥ የሀይድ መቆራረጥ ቢያጋጥማት በመካከል ላይ ያቆመበትን ጊዜ የንጽህና ጊዜ አድርጋ አትወስደውም። ለምሳሌ፡- የተለመደው የሀይድ ቆይታ 6 ቀን ቢሆን፣ በሶስተኛው ቀን ላይ ደሙ ቢያቆምና በአራተኛው ቀን ላይ ዳግም ቢከሰት የሶስተኛው ቀን በሀይድ እንጅ በንጽህና ጊዜ አይታሰብም። ይህ የሚሆነው ግን ደሙ በሚያቆምበት ወቅት የሀይድ ደም ሙሉ በሙሉ መቋረጥን የሚጠቁሙት ምልክቶች በዋነኝነትም ነጭ ዉሃ መሳይ ፈሳሽ እስካላየች ወይም አንድ ቀን ከነሌሊቱ ምንም አይነት ፈሳሽ እስካላጋጠማት ድረስ ነው። ተቻኩሎ መታጠብ አያስፈልግም።

◆ كانت عائشة رضي الله عنها تقول : لاتعجلن حتى ترين القصة البيضاء. رواه البخاري تعليقا ومالك موصولا

22. ትክክለኛው ሀይድ ከመጀመሩ በፊት የሚፈስ ደፍረስ ያለ ወይም ወደ ቢጫነት ያደላ ፈሳሽ ከሀይድ አይቆጠርም። በተመሳሳይ መልኩ የዚሁ አይነት ቀለም ያለውን ደም ያየችው ከታጠበች በኋላም ከሆነ በሀይድ ደም አይታሰብም። ነገር ግን

ይህ ፈሳሽ የተከሰተው በሀይድ ወቅትና ከመታጠቧ ቀደም ብሎ ከሆነ ከሀይድ ይመደባል።

◆ عن أم عطية رضي الله عنها قالت: كنا لا نعد الكُدرة والصُّفرة شيئًا. زاد أبو داود: "بعد الطُّهْر"، رواه البخاري

ሀይድ ላይ ላለች ሴት የተፈቀዱ ጉዳዮች

1) ሀይድ ላይ ያለች ሴት ከሀይድ ደሟ ዉጭ ነጃሳነት ያለው ምንም ነገር የለባትም። ምራቋ፣ ላቧ፣ መላ አካላቷ ሁሉ ንጹህ ነው። ሀይድ ላይ ካለች ሴት ጋር መሳሳም፣ መተቃቀፍ፣ አብሮ መብላት እና አብሮ መተኛት... ባጭሩ ከግንኙነት ዉጭ ያለን ማንኛውንም ጉዳይ መፈጸም እንደሚቻል የሚጠቁሙ ግልጽ ሀዲሶች እንድሁም የዑለማኦች ሙሉ ስምምነቶችም አሉ።

◆ عن أمَّ سَلَمَةَ رضي الله تعالى عنها قالَتْ: حِضْتُ وأنَا مَعَ النَّبيِّ ﷺ فِي الخَمِيلَةِ، فَانْسَلَلْتُ فخَرَجْتُ مِنْهَا، فَأَخَذْتُ ثِيَابَ حِيضَتِي فَلَبِسْتُهَا، فقالَ لِي رَسُولُ اللَّهِ ﷺ: أَنُفِسْتِ قُلْتُ: نَعَمْ، فَدَعَانِي، فَأَدْخَلَنِي مَعَهُ فِي الخَمِيلَةِ. رواه مسلم

◆ عن عائشة قالت : كنت كنت أشرب وانا حائض ثم أناوله النبي فيضع فاه على موضع في فيشرب ، وأتعرق العرق وانا حائض ثم أناوله النبي فيضع فاه على موضع في. رواه مسلم

2) ሀይድ ላይ ያለች ሴት የተለያዩ ልብሶችንና እቃዎችን ማጠብ፣ ምግብን ማዘጋጀት ወይም እጆቿን ፈሳሽነት ባላቸው ነገራቶች ዉስጥ መጨመር ትችላለች። ይሄን በማድረጓም የሚነጀስ አንድም ነገር የለም። ይህ የዑለማኦች ስምምነት ከተገኘባቸው ነጥቦች ዉስጥ ነው።

◆ عن مَيْمُونَةَ زَوْجَ النَّبِيِّ ﷺ : أَنَّهَا كَانَتْ تَكُونُ حَائِضًا، لاَ تُصَلِّي، وهِيَ مُفْتَرِشَةً بِحِذَاءِ مَسْجِدِ رَسُولِ اللَّهِ ﷺ وَهُوَ يُصَلِّي عَلَى خُمْرَتِهِ إِذَا سَجَدَ أَصَابَنِي بَعْضُ ثَوْبِهِ. رواه البخاري

◆ عن عائشة رضي الله عنها قالت : كان رسول الله يخرج إلي رأسه من المسجد وهو مجاور فأغسله وأنا حائض. رواه البخاري

3) ሀይድ ላይ ያሉ ሴቶች የዒድ ሶላቶች ወደ ሚሰገዱባቸው በታዎች መሄድ፣ የዒድ ተክቢራዎችን ማለት፣ የአማኞችን ዱዓእ በረከት መጋራት ይኖርባቸዋል። ባይሆን ግን ሶላቱ ላይ አይሳተፉም፣ የሚቀመጡትም ከሰጋጆቹ ሴቶች ሶፍ በኋላ ነው።

◆ عن أم عطية قالت " أمرنا رسول الله ان نخرجهن في الفطر والأضحى العواتق والحيض وذوات الخدور ، فأما الحيض فيعتزلن الصلاة ويشهدن الخير ودعوة المسلمين " رواه مسلم

ሀይድ ላይ ላለች ሴት የተከለከሉ ጉዳዮች

1. ሶላት

1. ሀይድ ላይ ያለች ሴት ግዴታም ይሁን ተጨማሪ የሆኑ ሶላቶችን መስገድ አትችልም፡፡ ብትሰግድም የምታገኘው አንዳችም አጅር የላትም፡፡ ይልቁንም የአላህን ክልከላ ተላልፋ በመስገዷ ወንጀለኛ ነች፡፡ የጌታዋን ክልክላ በማክበር ከሶላት ብትቆጠብ ግን አጅር ታገኝበታለች።

- عن ابي سعيد الخدري رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: .... أليس إذا حاضت لم تصل ولم تصم؟ فذلك نقصان دينها. رواه البخاري
- قال النووي في شرح مسلم: أجمع المسلمون أن الحائض والنفساء لا تجب عليهما الصلاة ولا الصوم في الحال"

2. በሀይድ ምክንያት ያለፏትን ሶላቶች ቀዷእ ማውጣት አይጠበቅባትም፡፡ ቀዷእ ብታወጣም ተቀባይነት የለውም፡፡ እንዳውም ሸሪዓው ያልደነገገውን በመፈጸሟ ተጠያቂነት አለባት፡፡ በሀይድ ምክንያት ያለፉ ሶላቶችን ቀዷእ ማውጣት ኸዋሪጅ የተባሉት የጥፋት አንጃዎች መለያ ነው።

- قالت عائشة رضي الله عنها: كان يصيبنا ذلك فنؤمر بقضاء الصوم ولا نؤمر بقضاء الصلاة. متفق عليه

3. አንድት ሴት የሶላት ወቅት ከገባ በኋላ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ሶላቱን ከመስገዷ በፊት የሶላቱ ወቅት ሳያልፍ ሀይድ ቢያጋጥማት ያንን ሶላት ቀዷእ መስገድ አይጠበቅባትም። ይህ የሀነፊያዎች እና የማሊኪያዎች ምርጫ ነው። ኢብኑ ተይሚያም ይሄንኑ ነው የሚያጠናክሩት። ምሳሌ፡- ዙህርን አዘግይታ ለመስገድ አቅዳ ከመስገዷ በፊት ሀይድ ቢያጋጥማት ይሄን ሶላት ቀዷእ ማውጣት አለባት የሚሉ ምሁራኖች ቢኖሩም ትክክለኛና ግልጽ መረጃ የላቸውም። ቀዷእን መደንገግ አድስ ሸሪዓዊ መመሪያን መደንገግ ስለሆነ ትክክለኛና ግልጽ መረጃ ያስፈልገዋል።

4. በንጽህናዋ ወቅት የረሳችው ሶላት መኖሩን ሀይድ ከጀመራት በኋላ ብታስታውስ ያንን ሶላት መስገድ የምትችለው ከሀይድ ከነጻች በኋላ ነው። ምሳሌ፡- ዙህር ሶላት አለመስገዷን የዙህር ወቅት አልፎ ሀይድ ከጀመራት በኋላ ብታስታውስ ከስድስት ወይም ከሰባት ቀን (ከታጠበች) በኋላ ትሰግደዋለች።

5. አንድት ሴት የነጻችው በሆነ ሶላት ወቅት ላይ ከሆነ ወቅቱን ያገኘችውን ሶላት ብቻ እንጅ ሌላን ሶላት እንድትሰግድ አትታዘዝም። ሶላቱ ምንም ይሁን ምን ሀይድ ላይ በነበረችበት ጊዜ ወቅቱ እስካለፈ ድረስ ያንን ሶላት እንድትሰግድ የሚያስገድድ ምንም አይነት መረጃም ምክንያትም የለም። ለምሳሌ: በዐስር

ወቅት ላይ የጸዳች ሴት ከዐስር ሶላት ዉጭ ሌላ ምንም አይነት ሶላትን መስገድ አይመለከታትም። በዐስር ወቅት የጸዳች ዙህርን፣ በዒሻእ ወቅት የጸዳች መግሪብን መስገድ ይጠበቅባታል የሚል እይታ ያላቸው ከፊል ሰለፎች እንድሁም ምሁራኖች ቢኖሩም ሃሳባቸው ግን ከትክክለኛና ግልጽ መረጃ የራቀ፣ በደካማ መረጃዎች ላይ የተደገፈ እንድሁም ግልጽ የሆኑ መረጃዎች ጋር የሚጣረስ ነው። ይህ (መስገድ የለባትም የሚለው አቋም) የሀነፊያዎች፣ የዟሂሪያዎች፣ በዘመናችንም የሸይኽ ዑሰይሚኒ አቋም ነው። በዚህም መሰረት ከእኩለ ሌሊት በኋላ የጸዳች ሴት መግሪብንም ይሁን ዒሻእን መስገድ አይጠበቅባትም ማለት ነው።

6. ሀይድ ማጠናቀቋን ያረጋገጠችው በሆነ ሶላት የመጨረሻ ወቅት (አንድ ሙሉ ረከዓ መስገድ በሚያስችል ወቅት) ላይ ቢሆንና እስከምትተጣጠብ ድረስ ወቅቱ ቢያልፍ ታጥባ እንዳጠቀቀች ያለፋትን ሶላት ትሰግዳለች። ሶላቷም በጊዜው እንደተሰገደ ነው የሚቆጠረው።

◆ عن أبي هريرة ان رسول الله قال: من أدرك ركعة من الصلاة فقد أدرك الصلاة. رواه البخاري

2. ጾም

1) ሀይድ ላይ ያለች ሴት መጾም አይፈቀድላትም። ብትጾምም ጾሟ ተቀባይነት የለውም። እንዳውም የአላህን ክልከላ በመተላለፏ ወንጀለኛ ትሆናለች።

◆ عن ابي سعيد الخدري رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: .... أليس إذا حاضت لم تصل ولم تصم؟ فذلك نقصان دينها. رواه البخاري

2) በሀይድ ምክንያት ያለፏትን የጾም ቀናቶች ቀዷእ የማውጣት ግዴታ አለባት። ማውጣቱም አይፈቀድም።

◆ قالت عائشة رضي الله عنها: كان يصيبنا ذلك فنؤمر بقضاء الصوم ولا نؤمر بقضاء الصلاة. متفق عليه

3) በረመዳን ጾም ላይ ሆና ጳሀይ ከመጥለቁ ከደቂቃም በፊት ቢሆን የሀይድ ደም ያጋጠማት ሴት ያንን ቀን ቀዷእ የማውጣት ግዴታ አለባት። አንድ ደቂቃ ሲቀረው ስለሆነ ሀይድ ያጋጠመኝ ጾሜ አይፈርስም የሚል ስሌት ተቀባይነት የለውም።

4) በረመዳን ቀን ላይ የጾዳች ሴት ሀይድ ካቆመበት በኋላ ያለውን የቀኑን ክፍለ ጊዜ ከምግብ፣ መጠጥና መሰል ጾመኛን ከሚያስፈጥሩ ነገራቶች ሁሉ መቆጠብ አለባት የሚል እይታ ያላቸው ምሁራኖች ቢኖሩም ተቀባይነት ያለው መከራከሪያ

ሃሳብ የላቸውም። በረመዳን ላይ ሴቶች ወይ ጾመኞች ወይም አፍጣሪዎች ናቸው። በሁለቱ መካከል የሚገኝ ከፊል ጾመኛ የሚባል ነገር የለም። ስለዚህ በጧቱ ክፍለ ጊዜ በሀይድ ላይ የሆነች ሴት በሰአቱ ክፍለ ጊዜ ብትጸዳ ምግብም መጠጥም… መጠቀም ትችላለች። ከጸዳች በኋላ የረመዳንን የቀኑን ክፍለ ጊዜ የማክበር ግዴታ አለባት የሚል መከራከሪያ አሳማኝ አይደለም። ራስን በመጥፎ ላለማስጠርጠር፣ ሌሎችን ላለማደፋፈር ከማሰብ የተነሳ ከሰዎች እይታ ራቅ ብላ መብላትና መጠጣቷ ግን ተገቢ ነው።

◆ قال ابن عثيمين رحمه الله: والقاعدة على هذا القول الراجح، أن من أفطر في رمضان لعذر يبيح الفطر، ثم زال ذلك العذر أثناء النهار لم يلزمه الإمساك بقية اليوم. فتاوى الصيام

5) ከፈጅር በፊት የጸዳች ሴት ከሀይድ ባትታጠብም እንኳ ጾም መያዝ ትችላለች። መጾምም አለባት። ይህ የአብዛኛዎቹ ምሁራኖች ሃሳብ ነው። ጾም ለመጾም የሀይዱ መቋረጥ እንጅ መታጠቡ እንደ ቅድመ ሁኔታ አይወሰድም።

3. ሀጂ

1. ሃይድ ላይ ያለች ሴት ለሀጂም ይሁን ለዑምራ ኢህራም ማድረግ ትችላለች። ኢህራም ለማድረግ መታጠብ ሱንና ስለሆነ ታጥባ መፈጸሟም ይወደድላታል።

- عن جابر رضي الله عنه: ان نبي صلى الله عليه وسلم قال لعائشة لما قدمت المكة وهي حائض: وأهلي بالحج. رواه مسلم
- عن عائشة رضي الله عنها قالت نفست أسماء بنت ابي عميس بمحمد بن أبي بكر بالشجرة فأمر رسول الله ابا بكر ان يأمرها ان تغتسل وتهل" رواه مسلم

2. ሀይድ ላይ ያለች ሴት ጠዋፈል ቁዱም፣ ጠዋፈል ኢፋዷ እንድሁም ጠዋፈል ወዳዕን መፈጸም አትችልም። ባጭሩ በከዕባ ዙሪያ መዞር አይፈቀድላትም።

- عَنْ عَائِشَةَ زَوْجِ النَّبِيِّ ﷺ أَنَّهَا قَالَتْ لِرَسُولِ اللهِ ﷺ: يَا رَسُولَ اللهِ، إِنَّ صَفِيَّةَ بِنْتَ حُيَيٍّ قَدْ حَاضَتْ؟ قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: لَعَلَّهَا تَحْبِسُنَا أَلَمْ تَكُنْ طَافَتْ مَعَكُنَّ؟، فَقَالُوا: بَلَى، قَالَ: فَاخْرُجِي . رواه البخاري
- قال ابن عبد البر في التمهيد: الحائض لا تطوف بالبيت وهو أمر مجمع عليه لا أعلم فيه خلافا.

3. ጠዋፈል ኢፋዷ (የመመለሻውን ጠዋፍ) ከፈጸምች በኋላ ሀይድ ያጋጠማት ሴት ጠዋፈል ወዳዕ (የስንብቱን ጠዋፍ) በመተው

ወደ ቤቷ ወይም ሀገሯ መመለስ ትችላለች። ሀጇም የተሟላ ነው፡

- عن ابن عباس رضي الله عنه قال: أمر الناس أن يكون آخر عهدهم بالبيت إلا أنه خفف عن الحائض. رواه مسلم
- عن عائشة قالت أن صفية بنت حيي زوج النبي صلى الله عليه وسلم حاضت في حجة الوداع, فقال النبي صلى الله عليه وسلم: أحابستنا هي؟ فقلت إنها قد افاضت يا رسول الله، وطافت بالبيت ، فقال النبي صلى الله عليه وسلم فلتنفر. رواه مسلم

4. በሀይድ ምክንያት ጠዋፈል ወዳዑን (የስንብት ጠዋፍ) ሳትፈጽም ወደ ሀገሯ በምትመለስበት ወቅት ከሀረም (መካ) ግዛት ርቃ ከመሄዷ በፊት ከሀይድ ከነጻች ወደ ከዕባ ተመልሳ ጠዋፈል ወዳዑን የመፈጸም ግዴታ አለባት። ነገር ግን የነጻችው የመካን ቤቶች ካለፈች በኋላ ከሆነ (ሶላትን መሰብሰብና ማሳጠር በሚፈቀድላት ቦታ ከደረሰች በኋላ ከሆነ) ተመልሳ ጠዋፈል ወዳዕን የመፈጸም ግዴታ የለባትም። ይህ የሀነፊያዎች፣ የሻፊዒያዎች እና የሀንበሊያዎች አቋም ነው።

- قال ابن قدامة في المغني (إذا نفرت الحائض بغير وداع ، فطهرت قبل مفارقة البنيان، رجعت فاغتسلت،وودعت،لأنها في حكم الإقامة....)
- وقال النووي مثل ماذكره ابن قدامة وزاد " وان كان بعد مسافة قصر لم يلزمها العود بلا خلاف: المجموع ٨/٢٥٥

5. በሀይድ ምክንያት ጠዋፈል ኢፋዷን መፈጸም ያልቻለች ሴት ከሀይድ እስከምትነጻ ድረስ መጠበቅና ከታጠበች በኋላ ጠዋፉን መተግበር አለባት። ምክንያቱም ጠዋፈል ኢፋዷ የሀጅ አንዱ መሰረታዊ ማእዘን (ሩክን) ስለሆነም በምንም መልኩ ቢሆን ሊቀር የሚችልበት አጋጣሚ የለም።

- عَنْ عَائِشَةَ زَوْجِ النَّبِيِّ ﷺ أَنَّهَا قَالَتْ لِرَسُولِ اللهِ ﷺ: يَا رَسُولَ اللهِ، إِنَّ صَفِيَّةَ بِنْتَ حُيَيٍّ قَدْ حَاضَتْ؟ قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: لَعَلَّهَا تَحْبِسُنَا... . رواه البخاري

6. ከሀይድ እስከምትነጻና ተጣጥባ ጠዋፈል ኢፋዷን እስከምትፈጽም ድረስ እንዳትቆይ የሚያደርጋት አስገዳጅ ምክንያት ካጋጠማት (ለምሳሌ መህረሟ ሊጠብቃት ፈቃደኛ ባይሆን፣ በሀይድ ምክንያት ለበርካታ ቀናት ለመቆየት የገንዘብ እጥረት ቢኖርባት፣ ስትዘገይ መጠለያ ቤት ማግኘት ባትችል፣ ሀገሯ ወይም ቤቷ ከተመለሰች በኋላ ዳግም የሌላ ጊዜ ሀጅ የማታደርግባቸው ምክንያቶች ቢኖሯት) ሀይድ ላይ እያለች ጠዋፈል ኢፋዷዋን መፈጸም ትችላለች የሚል እይታ ካላቸው ምሁራኖች ዉስጥ ኢብኑ ተይሚያህና ኢብኑል ቀይም በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ። ሸይኽ ኢብኑ ባዝም ይሄንኑ ሃሳብ ይመርጣሉ። የሚያቀርቧቸው መረጃዎች ግን ጥቅል የሆኑ ሸሪዐዊ መርሆዎችና ማመዛዘኛዎች (ቂያሶች) ናቸው።

◆ إن جميع الشروط والواجبات في العبادة معلقة بالقدرة ، فمن عجز عن تحقيق شرط او ركن أو واجب صار إلى البدل إن كان له بدل، وإن لم يكن له بدل سقط عنه . ولهذه القاعدة أدلة كثيرة من الكتاب والسنة

7. ሀይድ ላይ ያለች ሴት በሶፋ እና በመርዋ መካከል መሮጥ፣ ጠጠሮችን መወርወር፣ በዐረፋ ተራራ ላይ መቆም እና ሌሎችንም ከጠዋፍ ዉጭ ያሉ የሀጅ ስነስርአቶችን መፈጸም ይፈቀድላታል።

◆ عن عائشة وابن عباس رضي الله عنهما "الحائض تقضي المناسك كلها إلا الطواف بالبيت" رواه احمد

◆ عن عائشة رضي الله عنها أن انبي قال لها لما حاضت بالسرف " فاقضي مايقضي الحاج غير الا تطوفي بالبيت حتى تغتسلي رواه مسلم

4. ቁርአን መቅራት

1. ሀይድ ላይ ያለች ሴት በአእምሮዋ የሸመደደችውን ወይም የሚያቀራን ሰው በመከተል ቁርአን መቅራት ትችላለች። ምክንያቱም ኢብኑ ተይሚያህ እንደሚጠቅሱት ሀይድ ላይ ያለች ሴት ቁርአን ማንበቧን የሚከለክል አንድም ሶሂህ ሀዲስ የለም። ይህ የማሊኪያዎች፣ የዟሂሪያዎች፣ ቀዳሚው የኢማሙ ሻፊዒይ፣ የአህመድ ከፊል እይታ፣ የኢማሙ ቡኻሪይ፣ የኢማሙ አ'ጦበሪይ፣ የኢብኑ ተይሚያህ፣ የኢብኑል ቀይም፣ የኢብኑ ባዝ፣ የኢብኑ ዑሰይሚን፣ የአልባኒ እንድሁም የሳዑዲ ቋሚ የፈታዋ ኮሚቴ ምርጫ ነው።

2. በአራቱም መዝሀቦች ሀይድ ላይ ያለች ሴት ቁርአንን በእጆቿ በመንካት ማንበብ አትችልም። በርግጥ የተሸመደደን ማንበብ ከተቻለ መጽሀፉን መንካቱ የተለዬ ብይን እንድኖረው የሚያስገድድ ጉዳይ አይኖርም ነበር። ሀይድ ላይ ያለች ሴት ሶላት መስገዷን፣ ጾም መጾሟን በተመለከተ እንደተነገሩት ግልጽና ትክክለኛ ሀዲሶች፣ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ሀይድና ኒፋስ ላይ ያሉ ሴቶች ቁርአንን ማንበብም ይሁን መንካት አይችሉም የሚል ከልካይ መረጃ እስከሌለ ድረስ ሁሉም ሙስሊሞች በእኩል ደረጃ ቁርአንን ማንበብ ይችላሉ። ሆኖም ግን ከጭቅጭቅ ለመውጣት፣ ከስጋት ለመዳንም ሲባል በስልክና በኮምፒውተሮች በመታገዝ

ወይም በጓንት፣ በፎጣና በመሰል መከላከያዎች በመጠቀም ቁርአን ማንበብ መቻሏ የብዙ ምሁራኖች እይታ ስለሆነ ይሄንን መከተል የተሻለ ነው።

3. ሀይድ ላይ ባለች ሴት እግሮች መካከል ወይም እቅፍ ዉስጥ ሆኖ ቁርአን መቅራት ይቻላል። ነብዩም በዚህ መልኩ ይቀሩ ነበር።

- عن عائشة قالت: كان النبي صلى الله عليه وسلم يتكئ في حجري وأنا حائض ثم يقرأ القرآن. رواه البخاري

4. ሀይድ ላይ ያለች ሴት የትኛውንም አይነት ዚክርና ዱዓእ ማድረግን የሚከለክላት ምንም መረጃ ስለሌለ መፈጸም ትችላለች። ዱዐዎቹም ከቁርአን አንቀጾች የተመዘዙ ቢሆኑ ችግር የለውም።

5. አንዲት ሃይድ ላይ ያለች ሴት ቁርአንን በምታደምጥበት ወይም በምታነብበት ወቅት የማንበብ ሱጁድ (ሱጁደ ቲላዋ) ያለበትን አንቀጽ ብታደምጥ ወይም ብታነብ ሱጁደ ቲላዋ መፈጸም ትችላለች። አስደሳች ዜና ከሰማችም የምስጋና ሱጁድ ማድረግ ይፈቀድላታል። ምክንያቱም እነዚህ ሱጁዶች የሶላት አይነት ብይንም ይሁን የሶላት አይነት ቅድመ ሁኔታዎች የላቸውም።

◆ عن ابن عباس: أن النبي صلى الله عليه وسلم سجد بالنجم وسجد معه المسلمون والمشركون والجن والإنس" صحيح البخاري

5. መስጂድ መግባትና መቆየት

1) ሀይድ ላይ ያለች ሴት ለአስፈላጊ ጉዳይ በመስጂድ አቋርጣ መሄድ ትችላለች። ነገር ግን በምታልፍበት ጊዜ መስጅዱ ላይ ምንም አይነት ደም ሊያርፍ እንደማይገባ የታወቀ ጉዳይ ነው። መስጅድ ዉስጥ ጦሀራ የሆነውን ምራቅ መትፋትም ተከልክሏልና።

2) ሀይድ ላይ ያለች ሴት በመስጅድ ዉስጥ መቆይቷን በተመለከተ አራቱም መዝሀቦች ክልክል መሆኑን ይገልጻሉ። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ ዑለማኦች ይሄን አቋም ቢመርጡም ሀይድ ላይ ያለች ሴት መስጅድ መቆየት እንደማይፈቀድላት የሚጠቁም ትክክለኛ እና ግልጽነት ያለው መረጃ ግን የለም። ሁሉም ከልካይ ሀዲሶች ደካማ ናቸው። እንዳውም ሀይድ የሆነች ሴት መስጅድ መግባት እንደምትችል የሚጠቁሙ መረጃዎች (በቀጥታ ባይጠቁሙም) አሉ። መስጅድ ዉስጥ መቆየት ትችላለች የሚለው አቋም የኢብኑ ሀዝም፣ የዳውድ አዝዟሂሪይ፣ የኢማሙ ሙዘኒይ በዘመናችን ደግሞ የሸይኽ አልባኒ ጽኑ አቋም ነው። ለጥንቃቄ ሲባል አብዛኛዎቹ ዑለማኦች የመረጡትን አቋም መከተሉ አይከፋም። ለማስታወስ ያክል በዚህም ይሁን በሌሎች ክልከላዎች ላይ መረጃ እንድያቀርብ የሚጠየቀው ከልካዩ አካል እንጅ ፈቃጁ እንዳልሆነ በሰፊው የሚታወቅ መሰረታዊ መርህ

ነው። ስለዚህ መስጅድ ዉስጥ መቆየት ትችላለች የሚል አቋም ያለው አካል መረጃ መዘርዘር ባይጠበቅበትም ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩም ቢሆን ከታች ያሉት መረጃዎች መሰረታዊ የሆነውን የፊቅህ መርህ ደጋፊዎች ናቸው።

- عن عائشة رضي الله عنها قالت: قال لي رسول الله صلى الله عليه وسلم " ناولني الخمرة من المسجد؟ فقلت إني حائض. قال تناوليها ، فإن الحيضة ليست في يديك. رواه مسلم وأبو داود والنسائي
- قال النبي لعائشة إفعلي ما يفعل الحاج غير ألا تطوفي بالبيت حتى تطهري " رواه مسلم

- በርካታ ሰሀባዎች ጁኑብ ሆነው ዉዱእ ብቻ በማድረግ መስጅድ ያሳልፉ እንደነበረ ዐጧእ ቢን የሳር አስተላልፏል። ሀይድ ላይ ያለች ሴት ደግሞ ከጁኑብ ሰው በበለጠ መስጅድ እንድትገባ የሚያደርጓት ምክንያቶች አሏት።
- አንድት ጥቁር አገልጋይ በመስጅድ ዉስጥ የሆነች ድንኳን ተዘጋጅቶላት ረጂም ጊዜ መኖሯም ይሄንኑ ሀሳብ ያጠናክራል።
- ሙእሚን ንጹህ እንጅ ነጃሳ እንዳልሆነ የሚገልጸው ሀዲስም እንደ አጋዥ ተደርጎ ይወሰዳል።
- ሙሽሪኮችም መስጅድ የገቡበት አጋጣሚ መኖሩ ግልጽ ነው።

6. ግንኙነት መፈጸም

1. ሀይድ ላይ ያለችን ሴት መገናኘት ክልክል ነው፡፡ ይሄም በግልጽ የቁርአን አንቀጽና በትክክለኛ ሀዲስ እንድሁም በምሁራኖች ሙሉ ስምምነት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

◆ قال الله عز وجل "فاعْتَزِلُوا النِّسَاءَ فِي الْمَحِيضِ ولاَ تَقْرَبُوهُنَّ حَتَّى يَطْهُرْنَ" البقرة- ٢٢٢

2. አንድ ሰው በሀይድ ላይ ያለችን ሴት መገናኘት ይፈቀዳል የሚል እምነት ቢኖረው ወይም በዚህ እምነቱ ምክንያት ሀይድ ላይ ካለች ሴት ጋር ግንኙነት ቢፈጽም ከእስልምና ይወጣል፡፡ ማንኛውም ሃራምነቱ ላይ ምንም አይነት የምሁራኖች ልዩነት ያልተንጸባረቀበትን፣ በቀላሉ ተራው ሙስሊም ማህበረሰብ ሳይቀር የሚያውቀውን ጉዳይ ያስተባበለ ሰው ከእስልምና ለመውጣቱ ምሁራኖች ሁሉ በአንድ ድምጽ ተስማምተውበታል፡፡

◆ عن ابي هريرة رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: من اتى حائضا او أمرأة في دبرها او كاهنا فصدقه بما يقول ، فقد كفر بما انزل على محمد رواه أهل السنن وصححه الألباني

ነገር ግን ሀይድ ላይ ያለችን ሴት መገናኘት ሀራም መሆኑን ባለማወቁ ወይም ሀይድ ላይ መሆኗን ባለማወቁ ምክንያት

ግንኙነት ቢፈጽም ወንጀልም ይሁን የማካካሻ ቅጣት የለበትም።

3. ሀይድ ላይ ያለችን ሴት መገናኘት ሀራም መሆኑን ከማመኑ ጋር በማወቅና በምርጫው ግንኙነት የፈጸመ ግለሰብ ከተውበትና ከኢስቲግፋር በተጨማሪ ወንጀሉን የፈጸመው የሀይዷ የመጀምሪያው አካባቢ ከሆነ (ደሙ በብዛት በሚፈስበት ወቅት) አንድ ዲናር (4.15ግራም ወርቅ)፣ የመጨረሻዎቹ አካባቢ ከሆነ ደግሞ ግማሽ ዲናር ምጽዋት የማውጣት ግዴታ አለበት። ከፊል ምሁራኖች ደግሞ ይህ ቅጣት ከወር አበባዋ ሁኔታ ጋር ሳይሆን ከእሱ የመክፈል አቅም ጋር የተያያዘ ነው የሚልን ሀሳብ ሰንዝረዋል። የመክፈል አቅሙ ያለው ወንጀለኛ አንድ ድናር፣ የአቅም ዉስንነት ያለበት ከሆነ ደግሞ ግማሽ ድናር ይከፍላል ማለት ነው። ይህ ቅጣት በወንጀሉ ላይ ፈቃደኛ እስከሆነች ድረስ ሴቷንም በእኩል ደረጃ ይመለከታታል። ከታች የተጠቀሰውን ሀዲስ ኢብኑል ቀይም ትክክለኛ ብለውታል። ሸይኽ አልባኒ በርካታ መጽሀፍቶቻቸው ላይ ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው መሆኑን ገልጸዋል። ሸይኽ ኢብኑ ባዝም እንደዚሁ። ኢማሙ አህመድም በዚሁ መሰረት ብይን ይሰጡ ነበር።

◆ عن ابن عباس رضي الله عنهما عن رسول الله - صلى الله عليه وسلم - في الذي يأتي امرأته وهي حائض قال: يتصدق بدينار او بنصف دينار. رواه الخمسة وصححه الألباني في الإرواء

4. ባለቤቱ ሀይድ ላይ እያለች ግንኙነት ፈጽሞ የማካካሻ ቅጣቱን (ከፋራ) ካወጣ በኋላ ሌላ ግንኙነት ቢፈጽም ሌላ አድስ ከፋራ ማውጣት ያስፈልገዋል፡፡ ሁለተኛውን ግንኙነት የፈጸመው ለመጀመሪያው ከፍራ ሳያወጣ ከሆነ ደግሞ ለመጀመሪያው ከፋራ ያላወጣበት ምክንያት ሁለተኛ መፈጸምን አስቦ ከሆነ በፈጸመው ግንኙነት ልክ ተደራራቢ ከፋራ እንድያወጣ ይገደዳል፡፡ ይህም የሆነው ሸሪዓዊ ክልከላዎችን ለመተላለፍ የብልጠት አካሄድን መሄድ አይቻልምና ነው፡፡

5. ሀይድ ላይ የነበረች ሴት ግንኙነት መፈጸም የሚፈቀድላት ደሙ ካቆመበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ከታጠበችበት ጊዜ ጀምሮ ባለው ወቅት ለመሆኑ ከኢብኑ ሀዝም ዉጭ ያሉ ዑለማኦች ተስማምተዋል፡፡ የቁርአኑ መልእክትም ይሄንኑ ሀሳብ ነው የሚገልጸው፡፡

◆ { فإذا تطهرن فأتوهن من حيث أمركم الله} البقرة:٢٢٢

6. ሚስቱ ከመጽሀፍቱ ባለቤቶች (አህለል ኪታብ) ብትሆንም እስካልታጠበች ድረስ ግንኙነት መፈጸም አይፈቀድለትም፡፡

7. ሀይድ ላይ ካለች ሴት ጋር ደም ከሚፈስበት አካል ዉጭ ያለን (ከግንኙነት ዉጭ ያለን) ማንኛውም ቅርርብ መፈጸም ይቻላል፡፡

◆ عن أنس رضي الله عنه: قال عليه الصلاة والسلام: ... اصنعوا كل شيءٍ إلا النكاح... رواه مسلم

ነገር ግን ስሜቱን መቆጣጠር እንደማይችል ስጋት ያለው ሰው ሙሉ በሙሉ መራቅ ወይም ቢያንስ ከጉልበቷ እስከ እምብርቷ ድረስ ያለውን አካሏን መራቅ ይኖርበታል፡፡

8. ሚስትን ሀይድ ሲያጋጥማት ፍራሽን በመለየት ተራርቆ መተኛትን በተመለከተ የተላለፉ ሀድሶች በሙሉ ደካማዎች ናቸው፡፡

9. ሀይድ ላይ ያለች ሴት የትዳር አጋሯ አካሏን ቀጥታ እንዳይነካ የሚያግድን ልብስ (የሴት ቱታ፣ ቁምጣ፣ ታይት...) መልበስ ይወደድላታል፡፡

◆ عن عائشة: كانت إحدانا إذا كانت حائضا: فأراد رسول الله صلى الله عليه وسلم أن يباشرها، أمرها ان تتزر في فور حيضتها ثم يباشرها. وأيكم يملك إربه كما كان رسول الله يملك إربه. أخرجه مسلم

10. ሀይድ ላይ በነበረችበት ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ጁኑብ ብትሆን ከሀይድ የምትጸዳበትን ጊዜ ከምትጠብቅ ይልቅ ጀናባውን ለማስወገድ በማሰብ ጀነባ በሆነችበት ወቅት መታጠቧ ይወደድላታል።

7. ፍች

1) በሀይድ ላይ ያለችን ሴት መፍታት በጽኑ የተከለከለ ነው። መጤ ፍቺ (ጦላቀል ቢድዒይ) የሚል ስያሜም ተሰጥቶታል። በዚህም ላይ የምሁራኖች ስምምነት አለ።

◆ { يَا أَيُّهَا النَّبِيُّ إِذَا طَلَّقْتُمُ النِّسَاءَ فَطَلِّقُوهُنَّ لِعِدَّتِهِنَّ وَأَحْصُوا الْعِدَّةَ} الطلاق ١-

2) ሀይድ ላይ እያለች የተፈታችን ሚስት መመለስ ግዴታ ነው። ከመለሳት በኋላ መፍታት ከፈለገ ደግሞ ግንኙነት ባልፈጸሙበት የንጽህናዋ ወር ወይም በእርግዝና ላይ የምትሆንበት ጊዜ ጠብቆ መፍታት እንደሚችል ተገልጿል።

◆ عن ابن عمر انه طلق إمرأته وهي حائض فسأل عمر رسول الله وقال: مره فليراجعها حتى تطهر ثم تحيض حيضة أخرى ثم تطهر ثم يطلق بعد او يمسك. أخرجه مسلم

3) ሀራም ከመሆኑ ጋር ሚስት ሀይድ ላይ ባለችበት ወቅት ፍቹ ቢፈጸም ግን ፍቹ ይጸናል የሚለው እይታ የተሻለ ነው። የአብዛኛዎቹ ምሁራኖች ምርጫም ይሄው ነው። በርግጥ ይህ ጉዳይ በምሁራኖች መካከል እጅግ በጣም ከፍተኛ አለመግባባት ከታየባቸው የፊቅህ አጀንዳዎች ዉስጥ ይመደባል።

- عن ابن عمر انه طلق إمرأته وهي حائض فسأل عمر رسول الله وقال: (مره فليراجعها ثم ليطلقها طاهرا او حاملا) . رواه مسلم
- فقال ابن عمر (وحسبت علي بتطليقة) رواه البخاري

4) መመላለስ በሚያስችለው ፍቺ የተፈታች ሴት ባለቤቷ እንዳይመልሳት በማሰብ ሀይድ ማየት አለማየቷን ወይም መጸነስ አለመጸነሷን ወይም የሚገመተውን የመውለጃ ጊዜዋን መደበቅ ሃራም ተደርጎባታል።

- {وَلاَ يَحِلُّ لَهُنَّ أَنْ يَكْتُمْنَ مَا خَلَقَ اللهُّ فِي أَرْحَامِهِنَّ إن كن يؤمن بالله واليوم الأخير} البقرة: ٢٢٨

5) በሀይድ ላይ ያለችን ሴት መፈታት የሚቻልባቸው ሶስት ሁኔታዎች አሉ። እነሱም:-

- ✧ ኹልዕ (የፍች ጥያቄው ካሳ በመክፈል በራሷ ተነሳሽነት ከቀረበ) መረጃውም ኹልዕ ከፍቺ አለመቆጠሩ ነው።

- ✧ ሀይድ ያየችው በእርግዝናዋ ወቅት ላይ ከሆነ መፍታት ይቻላል። መረጃውም መልእክተኛው ለኢብኑ ዑመር በሀይድ ላይ እያለች የፈታትን ሚስቱን እንዲመልሳትና ከነጻች በኋላ ዳግም ሃይድ አይታ እንደነጻች ወይም እርግዝናዋ እንደተረጋገጠ ከፈለጋት እንድይዛት ካልፈለጋት ደግሞ እንዲፈታት መፍቀዳቸው ነው።

✧ ሀይድ ያየችው ከተጋባች በኋላና፤ ከባሏ ጋር ከሰዎች ተገልለው ከማሳለፋቸው በፊት ከሆነ መፍታት ይቻላል።

◆ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا نَكَحْتُمُ الْمُؤْمِنَاتِ ثُمَّ طَلَّقْتُمُوهُنَّ مِن قَبْلِ أَن تَمَسُّوهُنَّ فَمَا لَكُمْ عَلَيْهِنَّ مِنْ عِدَّةٍ تَعْتَدُّونَهَا :أحزاب -٤٩

6) ሀይድ ላይ ላይ ያለች ሴት ኒካህ ማድረግ ትችላለች። ምክንያቱም ይሄን የሚከለክል አንዳችም መረጃ የለም።

◆ قال ابن حزم في المحلى: جائز للحائض والنفساء ان يتزوجا.

ሀይድና ኒፋስ ላይ ያሉ ሴቶች ማግባት ይፈቀድላቸዋል ይላሉ ኢብኑ ሀዝም።

የሀይድ ማዘግያ ወይም ማፍጠኛ መድሀኒቶችን መጠቀም

- ጤናዋ ላይ የጎንዮሽ ተጽእኖ ወይም ጉዳት እስከሌለው፣ ባለትዳር ከሆነች ባለቤቷ እስከፈቀደላት ድረስ እንድሁም ሸሪዓዊ ድንጋጌዎችን ለማሳለፍ በማሰብ እስካልሆነ ድረስ ሀይድን የሚያፋጥን ወይም የሚያዘገይ መድሀኒት መጠቀም ይፈቀዳል።

◆ قال جابر كنا نعزل على عهد رسول الله فبلغ ذالك النبي فلم ينهانا. رواه مسلم

ከላይ የተጠቀሰው ሀዲስ ለወንዶች የዘር ፈሳሻቸውን ከሴቷ ብልት ዉጭ ማፍሰሱ የተፈቀደ ከሆነ ሴቷም ብትሆን ተመሳሳይ አገልግሎት ያላቸውን መድሀኒቶች መጠቀም ትችላለች ማለትን ይጠቁማል።

ሀይድ ማቆሙን ማረጋገጫ መንገዶች

የሀይድ ደም ማቆሙ በሶስት መንገድ ሊረጋገጥ ይችላል። ይሄውም:-

1) የሀይድ ደም መጠናቀቅን ተከትሎ ከማህጸን የሚለቀቅውን ዉሃማ ነጭ ፈሳሽ መፍሰስ አለመፍሰሱን በማረጋገጥ የሀይድን መጠናቀቅ ማረጋገጥ ይቻላል። ቀዳሚውና ከሁሉም የተሻለው ማወቂያ መንገድም ይሄ ነው። ነገር ግን ይህ ፈሳሽ በአንዳንድ ሴቶች ላይ ሙሉ በሙሉ ላይከሰት ይችላል። ለሌሎች ደግሞ የሚመጣው ዘግይቶ ሊሆን ይችላል።

- عن عائشة أن النساء كن يَبْعَثْنَ إلـيها بالدُّرَجَةِ فِيهَا الكُرْسُفُ فِيهِ الصُّفْرَةُ، فتَقُولُ: «لاَ تَعْجَلْنَ حَتَّى تَرَيْنَ القصَّةَ البَيْضَاءَ» تُرِيدُ بذلِكَ الطُّهْرَ مِنَ الحَيْضَةِ، وبلَغَ ابنة زَيْدِ بْنِ ثابتٍ رضي الله تعالى عنهما: أنَّ نِسَاءً يَدْعُونَ بِالْمَصَابِيحِ مِنْ جَوْفِ اللَّيْلِ يَنْظُرْنَ إِلَى الطُّهْرِ، فقالَتْ: "مَا كَانَ النِّسَاءُ يَصْنَعْنَ هَذَا، وعَابَتْ عَلَيْهِنَّ". فتح الباري في شرح صحيح البخاري

2) እንደጥጥ፣ ሱፍ ወይም መሰል ልብሶችን በመራቢያ አካል በመጨመር የሀይድ ደም መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ሀይድ መጨረስ አለመጨረስን ማረጋገጥ ይቻላል። ይሄን ከላይ ከተጠቀሰው መረጃ መረዳት ይቻላል።

3) አንድ ቀን ከነሌሊቱ ምንም አይነት ፈሳሽ ሳያጋጥማት ከቀረ ሀይድ እንደተጠናቀቀ በመውሰድ መንጻት ይኖርባታል። ይህ ከዘmeናችን ዑለማኦች የሸይኽ ዐብዱልዐዚዝ ቢን ባዝ እይታ ሲሆን ከቀደምቶች ደግሞ ኢብኑ ቁዳማ ተጠቃሾች ናቸው።

ኢስቲሀዷ (የበሽታ ደም)

- ኢስቲሀዷ (የበሽታ ደም) ከሀይድ ጋር ተያይዞ ወይም ሀይድ ከተጠናቀቀ በኋላ በሴት ልጅ ብልት በኩል በቋሚነት ያለምንም ማቋረጥ ወይም ከወሩ ዉስጥ ለረጅም ጊዜ (የወሩን አብዛኛውን ጊዜ) የሚፈስ ያልተለመደ ደም ነው፡፡

- ኢስቲሃዷ ከሀይድ ጋር ተያይዞ ካልቀጠለ ማወቁ በጣም ቀላል ነው፡፡ ሀይድ ጋር ተያይዞ ከተከሰተ ግን በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

- ኢስቲሀዷ ያጋጠማት ሴት ሶስት አይነት ሁኔታ ይኖራታል።

1) የታወቀ የሀይድ ኡደት ያላት ከሆነች ከረጅሙ የደም ፍሰት ዉስጥ የተለመደውን የሀይድ ጊዜ ለሀይድ በማሰብ ቀሪውን የደም ፍሰት በበሽታ ደም ታስበዋለች፡፡ ለምሳሌ ልጅቷ ኢስቲሃዷ ሳያጋጥማት በፊት የነበራት የሀይድ ኡደት ሁልጊዜም ለአምስት ቀን ቢሆንና ይሄም የሚከሰተው ወሩ በገባ በመጀመሪያዎቹ አምስቱ ቀናት ቢሆን የኢስቲሀዷ ደም ካጋጠማት በኋላም እያንዳንዱ ወር ሲገባ የመጀመሪያዎቹን አምስት ቀናቶች በሀይድ ታስባቸውና ከሀይድ ትታጠባለች፡፡ ከዚያ በኋላ ያለውን የደም ፍሰት ከበሽታ ደም በመቁጠር ከሀይድ ንጹህ የሆነች ሴት የምትፈጽመውን ሁሉ

ትፈጽማለች፡፡ ይህ ለክትትል በጣም ቀላሉ፣ ከመረጃዎችም ብዛትና ጥንካሬ አንጻር የተሻለው መለያ መንገድ ነው፡፡ ይህ የአብዛኛዎቹ ኡለማኦች አቋም፣ የአቡሀኒፋ፣ የሻፍዒይና የአህመድ መዝሀብ፣ የኢብኑ ተይሚያህ፣ የአልባኒ፣ የኢብኑ ዑሰይሚንና የሌሎችም ተቀዳሚ ምርጫ ነው፡፡

◆ قال النبي عليه الصلاة والسلام لأم حبيبة " امكث قدر ما كانت تحبسك حيضتك ثم اغتسلي وصلي" رواه مسلم

2) የሀይድ ሁኔታዋ የተዘበራረቀ በመሆኑ ምክንያት የታወቀ የሀይድ ኡደት የሌላት ከሆነችና የሀይድንና የኢስቲሀዷን ደም ግን ለይታ ማወቅ ከቻለች የደሙን ሁኔታ በመከታተል የሀይድ ደም መገለጫዎች ሲኖሩ በሀይድ በማሰብ የሀይድነት ባህሪ የሌለው ደም ሲፈሳት ደግሞ የኢስቲሀዷ ደም በማድረግ ትወስደዋለች፡፡ ለምሳሌ ጠቆር ያለ፣ መጥፎ ጠረን ያለው እንድሁም ሙቀት የሚፈጥር ደም ሲሆን በሀይድ ትወስደዋለች ከዚህ ውጭ (ቀይ ሲሆን፣ መጥፎ ጠረን ከሌለው፣ የሞቃትነት ስሜት ካልፈጠረ፣ የጠጣርነት ባህሪ ያለው ከሆነ ደግሞ በኢስቲሀዷ ትወስደዋለች ማለት ነው፡፡

◆ قال النبي لفاطمة بنت ابي حبيش " إذا كان دم الحيض فإنه دم أسود يعرف فإذا كان ذالك فأمسكي عن الصلاة ، فإذا كان الآخر، فتوضئي إنما ذالك عرق " رواه ابو داود والنسائي وصححه الألباني

3) ከላይ ያሉትን ሁለቱን ሁኔታዎች ካላሟላች ደግሞ አብዛኛዎቹ ሴቶች የሚያጋጥማቸውን የሀይድ የጊዜ ቆይታ ለራሷ በመውሰድ በሀይድ ታስባቸዋለች፡፡ ለምሳሌ ሀይድ በአብዛኛዎቹ ሴቶች ላይ የሚቆየው ለስድስት ወይም ለሰባት ቀናት ስለሆነ ከረጅሙ የደም ፍሰቷ ዉስጥ ስድስቶቹን ወይም ሰባቶቹን ቀናቶች በሀይድ በማሰብ ትጸዳና ከዚይ በኋላ የሚፈሰውን ደም በኢስቲሀዷ ደም ትቆጥራቸዋለች ማለት ነው፡፡

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لحمنة بنت جحش: ---- إنما هذه ركضة من ركضات الشيطان، فتحيضي ستة ايام او سبعة ايام في علم الله ثم اغتسلي... رواه اصحاب السنن إلا النسائي وصححه الألباني

4) ምንም አይነት ሀይድ ሳታይ ለመጀመሪያ ጊዜ ረጂም የደም ፍሰት ያጋጠማት ሴት በሁለቱ ደሞች መካከል መለየት ከቻለች በእሱ መሰረት የሀይድንና የኢስቲሀዷን ደም ለይታ ለሁለቱም የተደነግጉትን ህግጋቶች ትተገብራለች። ደሙ የሀይድ ይሁን የኢስቲሀዷ ይሁን መለየት ካልቻለች ግን በሀይድ ትቆጥረዋለች። እንደብዙሀኖች ምሁራኖች ምርጫ ከፍተኛው የሀይድ የጊዜ ቆይታ ላይ (15 ቀን) ከደረሰ ግን ሰውነቷን ታጥባ ቀጣዩን የደም ፍሰት የኢስቲሀዷ ደም አድርጋ ትወስደዋለች።

5) ኢስቲሀዷ ላይ ያለች ሴት የተለመደው የሀይድ ጊዜዋ ስድስት ወይም ሰባት ቀን መሆኑን ብታውቅ ነገር ግን በትክክል የትኛው

ቁጥር እንደሆነ መለየት ቢሳናት ለጥንቃቄ ሲባል ሰባቱን ቀናት የሀይድ ቀናት አድርጋ ትይዛቸዋለች።

6) በተመሳሳይ መልኩ የተለመደው የሀይድ ጊዜዋ ወር በገባ በመጀመሪዎቹ ቀናቶች መሆኑን ብታውቅ ነገርግን ስንተኛው ቀን ላይ እንደሚጀምራት ባታስታውስ ከወሩ መጀመሪያ መነሳቷ ትክክለኛ ምርጫ ነው።

7) የሀይድ ጊዜዋ ለምን ያክል ቀን እንደሚቆይ እያወቀች ነገር ግን ከስንተኛው ቀን ላይ እንደሚጀምራት ማስታወስ ያልቻለች ሴት የደም ፍሰቱን የመጀመሪያዎቹን ቀናቶች ለሀይድ ጊዜ አድርጋ በመውሰድ ከታጠበች በኋላ ቀሪውን ጊዜ በኢስቲሀዷ መቁጠሯ የተሻለ ነው። ምክንያቱም መሰረታዊ በሆነው መርህ መሰረት ሴት ልጅ የሚያጋጥማት ደም በዋነኝነት የሀይድ ደም ተደርጎ ነው የሚወሰደው።

ኢስቲሀዷ ላይ ያለች ሴት ምን ይጠበቅባታል?

- ከላይ በተገለጹት ነጥቦች መሰረት ለሀይድ የሰጠችውን ጊዜዋን ካጠናቀቀች በኋላ ሀይድ ላይ የነበረች ሴት በምትጸዳዳበት መልኩ መላ አካላቷን ትታጠባለች። ከዚያም በኋላ ደሟ እየፈሰሰ ሰውነቷንና ሌሎች ነገራቶችን እንዳይነካ የሴቶችን የንጽህና መጠበቂያ ልብሶች ትጠቀማለች። ከታጠበች በኋላ ለማንኛውም ንጹህ ሴት የተደነገገው ሁሉ ለእሷም የተደነገገ ይሆናል። ሶላት መስገድ፣ ጾም መጾም ፣ ጦዋፍ ማድረግ。。。 ይፈቀድላታል ማለት ነው።

ኢስቲሀዷ ላይ ያለች ሴት ሶላት አሰጋገድ

1) ለእያንዳንዱ ሶላት ዉዱእ ማድረግ ይኖርባታል፡፡ ለምሳሌ ዙህርን ለመስገድ የዙህር ወቅት ሲገባ ዉዱእ ታደርጋለች፡፡ የዱሃ ሶላትን ለመስገድም ስታስብ አድስ ዉዱእ ማድረግ ይጠበቅባታል ማለት ነው። ደም እስከፈሰሳት ድረስ ኢስቲንጃእ ማድረግ እንደሚያስፈልጋትም ግልጽ ነው፡፡ ይህ የሻፊዒይና የአህመድ አቋም ነው። ሸይኽ አልባኒም ይሄን ይመርጣሉ። ለዙህር ሶላት ባደረገችው ዉዱእ ዙህርን፣ የዙህርን ሱንናዎች እንድሁም በጥቅሉ ሌሎች ዉዱእ አፍራሽ ነገራቶች እስካላጋጠሟትና የዐስር ሶላት ወቅት እስከሚገባ ድረስ የትኛውንም አይነት ሶላት መስገድ ይፈቀድላታል የሚሉት ደግሞ ሀነፊያዎች ናቸው። ኢብኑ ባዝም ከዚህ አቋም ጎን ይሰለፋሉ፡፡ ማሊኪያዎች ደግሞ ለእያንዳንዱ ሶላት ዉዱእ ማድረግ እንዳለባት የሚገልጹ ሀዲሶች በሙሉ ደካማዎች፣ እርስበርሳቸው የማይስማሙ፣ ወጥነት የሌላቸው፣ የተምታቱ ሀዲሶች ስለሆኑ ለሁሉም ሶላት በተናጠል ዉዱእ ማድረግ የሚወደድ ተግባር እንጅ ግዴታ አይደለም ይላሉ። ኢብኑ ዑሰይሚኒም ይሄንን ሃሳብ ይጋራሉ። ለጥንቃቄም ሲባል ቢሆን የመጀመሪያውን አቋም መከተል በጣም አዋጭ ነው።

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لعائشة " مري فاطمة بنت ابي حبيش فلتمسك كل شهر عدد ايام أقرائها ، ثم تغتسل وتحتشي وتستثفر وتنظف ، ثم تطهر عند كل صلاة وتصلي" أخرج أحمد ودارقطني وإستدل به الألباني في ثمر المستطاب وقال في الباب احاديث أخرى.

2) ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ዙህርን በማዘግየትና ዐስርን በማፋጠን የሁለቱ ሶላቶች መገናኛ ወቅት ላይ ሰውነቷን ታጥባ ሁለቱንም ሶላቶች በተቀራራቢ ሰአት አስከታትላ መስገድ ትችላለች፡፡ ለመግሪብና ለዒሻእም ተመሳሳይ አፈጻጸምን ትከተላለች፡፡ የሱብሂ ሶላት ግን ከየትኛውም ሶላት ጋር መሰባሰብ ስለማይችል ለብቻው ሰውነቷን ታጥባ ትሰግዳለች፡፡ ይህ የሚወደድ ተግባር እንጅ ግዴታ አይደለም።

◆ ففي حديث أسماء بنت عميس، قال رسول الله صلى الله عليه وسلم لفاطمة بنت أبي حبيش: فإذا رأت صفرة فوق الماء فلتغتسل للظهر والعصر غسلا واحدا، وتغتسل للمغرب والعشاء غسلا واحدا وتغتسل للفجر وتتوضأ فيما بين ذالك " أخرجه حاكم وصححه شيخ الألباني

3) ሶስተኛው አማራጭ ለእያንዳንዱ ሶላት ለየብቻቸው መላ ሰውነቷን እየታጠበች መስገድም ትችላለች፡፡ ግዴታ ግን አይደለም። ምክንያቱም ፋጢማ ቢንት አቢ ሁበይሽ ከራሷ ተነሳሽነት እንጅ ነብዩ አዘዋት አልፈጸመችውም።

◆ عَنْ عَائِشَةَ، أنَّ فاطِمَةَ بِنْتَ أبي حُبَيْشٍ رضي الله تعالى عنها سَألَتِ النَّبيَّ ﷺ قالَتْ: إنِّي أُسْتَحَاضُ فلا أطْهُرُ، أفأدَعُ الصَّلاَةَ؟ فقالَ: لاَ إنَّ ذَلِكِ عِرْقٌ، ولَكِنْ دَعِي الصَّلاَةَ قدْرَ الأيَّامِ الَّتِي كُنْتِ تَحِيضِينَ فِيهَا، ثُمَّ اغْتَسِلِي، وصلِّي: فكَانَتْ تَغْتَسِلُ لِكُلِّ صلاَةٍ.

- በበሽታ ደም የተጠቃች ሴት ዉዱእ ካደረገች በኋላ ሶላት እስከምትሰግድ ድረስ የሚፈሰው ደም በዉዱእዋ ላይ ምንም አይነት ተጽእኖ አያሳድርባትም። ሶላት በምትሰግድበት ወቅት ደሙ ቢንጠባጠብ ራሱ ሶላቷም ላይ ይሁን ዉዱእዋ ላይ የሚኖረው ጉዳት የለም። የንጽህና መጠበቂያ መጠቀሟ ግዴታ መሆኑን የሚጠቁሙ ትክክለኛ ሀዲሶች ስላሉ አቅም የፈቀደውን መጠቀም ግድ ይላል።

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لفاطمة بنت ابي حبيش "وتوضئي لكل صلاة وإن قطر الدم على الحصير" رواه ابن ماجه

◆ عن عائشة قالت: إعتكفت مع رسول الله صلى الله عليه وسلم إمرأة من ازواجه فكانت ترى الدم والصفرة والطست تحتها وهي تصلي. رواه البخاري

- ኢስቲሀዷ ላይ ያለች ሴት ግንኙነት መፈጸምን የሚከለክላት ምንም አይነት ትክክለኛ እና ግልጽ መረጃ ስለሌላ መፈጸም የተፈቀደ ነው። መረጃም ተገኝቶለታል።

◆ سئل سعيد بن جبير: اتجامع المستحاضة ؟ فقال: الصلاة أعظم من الجماع" روه الدارمي

◆ عن عكرمة قال: كانت أم حبيبة تستحاض فكان زوجها يغشاها. صحيح سنن ابي داود

በማህጸን ቁስለት ወይም በህክምና ምክንያት የሚፈስ ደም ከሀይድም ይሁን ከኢስቲሀዷ አይመደብም። ስለዚህ ይህ ደም እንደማንኛውም ዉዱእ አፍራሽ ነገር ብቻ ነው የሚቆጠረው። በርግጥ ሸይኽ ዑሰይሚኒ የዚህ አይነት የደም ፍሰት ያጋጠማት ልክ ኢስቲሀዷ ላይ እንዳለች ሴት ለእያንዳንዱ ሶላት ዉዱእ ማድረግ ይጠበቅባታል የሚል እይታ አላቸው።

ኒፋስ (የዉልደት ደም)

- ኒፋስ ቋንቋዊ ትርጓሜው ደም፣ ከጭንቅ መገላገል፣ ነፍስ ያለውን ልጅ ማግኘት፣ የማህጸን ባዶ መሆን ማለት ሲሆን ሸሪዓዊ ትርጉሙ ደግሞ በመውለድ ወይም የመውለጃ ጊዜ በመቃረቡ ምክንያት ከማህጸን የሚለቀቅና በሴት ልጅ መራቢያ አካል በኩል የሚፈስ ደም ነው።

- ልጅ ከመወለዱም ቀደም ብሎ ቢሆን የደሙ ፍሰት ከምጥ ጋር ተያይዞ ከጀመረ የኒፋስ ደም ተደርጎ ይወሰዳል።

የኒፋስና የጊዜ ትስስር

- በብዛት የሚከሰተውና በሰፊው የተለመደው እንድሁም በበርካታ መረጃዎችም የሚደገፈው አቋም የኒፋስ ደም ረጅሙ የጊዜ ገደብ አርባ ቀን ነው የሚለው ነው። ይህ የኢብኑ ዑመርና የኢብኑ ዐባስም رضي الله عنهم አቋም ነው። የሀነፊያዎችና የሀንበሊያዎችም መዝሀብ ነው። የኢብኑ ሙንዚር፣ የሸውካኒ፣የኢብኑ ባዝ፣ የአልባኒ እንድሁም የሳዑዲ ቋሚ የፈተዋ ኮሚቴም ምርጫ ይሄው ነው። በህክምናውም ቢሆን የውልደት ደም ለስድስት ሳምንታት ሊቀጥል ይችላል። ስለዚህ አርባ ቀን ድረስ ካልጸዳች ከዚያ በኋላ የሚፈሰውን ደም በኢስቲሀዷ ትወስደውና ትጸዳለች። ይህ የተሻለውና ከመረጃም አንጻር

ተመራጩ አቋም ነው። የኒፋስ ደም እስከ ስልሳ ቀን ድረስ ይቀጥላል የሚሉም አሉ።

- عن ابن عباس: تنتظر النفساء اربعين يوما. أخرجه الدارمي قال الألباني سنده صحيح على شرط الستة
- أم سلمة رضي الله عنها قالت: كانت النفساء تقعد على عهد رسول الله ﷺ أربعين يومًا. أخرجه أهل السنن وصححه الألباني

- የኒፋስ ደም አነስተኛ የጊዜ ገደብ የለውም። ስለዚህ አንዷት ሴት ከወለደች ከደቂቃዎች በኋላ ጀምሮ ደሙ ቢያቆምላት ወዲያዉኑ ተጣጥባ ማንኛውንም ሸሪዓዊ ትእዛዛት (ሶላት፣ጾም...) የመፈጸም ግዴታ ይኖርባታል። ይህ የሻፊዒይ፣ የኢብኑ ተይሚያህ፣ የኢብኑ ሀዝም፣ የኢብኑ ባዝ፣ የዑሰይሚኒና የአልባኒ ምርጫ ነው። ደረጃቸው ደካማ ቢሆንም ተደጋግፈው መረጃ መሆን የሚችሉ በርካታ ሀዲሶች አሉ።

- ኒፋስ ላይ ያለች ሴት አርባ ቀኑን ከማጠናቀቁ በፊት ደሙ በማቆሙ ምክንያት ታጥባ ከተወሰነ የጊዜ ቆይታ በኋላ ዳግሞ ተመልሶ ቢያጋጥማት የደሙ ፍሰት የተከሰተው በአርባ ቀናቶቹ ዉስጥ ከሆነና ከማርገዟ በፊት ሀይድ በምታይበት ወቅት ላይ ከተከሰተ በሀይድ መቁጠሯ፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ በኒፋስ ደም መውሰዷ የተሻለው ምርጫ ነው።

- የኒፋስ ደም የጊዜ ገደብ መነሻ ተደርጎ የሚወሰደው ከወለደች በኋላ ያለው ጊዜ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድት ሴት በምጥ ሰአት ላይ የሚፈሳትን ደም ከአርባ ቀናቶቹ ዉስጥ አትቆጥረውም ማለት ነው፡፡

- መንታ ልጆችን የወለደች ሴት የኒፋሷን ጊዜ የምታሰላው የመጀመሪያው ልጅ ከተወለደበት ሰአት ነው የሚለው የብዙዎች ምርጫ ነው፡፡ ሁለተኛው ልጅ ከተወለደበት ቀን ነው የሚለው ግን የተሻለ ነው። ምክንያቱም ኒፋስ የሚለው ቃል በከፊል ትርጉሙ የማህጸን ባዶ መሆን ነው። ሁለተኛው ልጅ እስካልተወለደ ድረስ እርጉዝ ሴትም ተደርጋ ነው የምትቆጠረው። መንታ ልጆችን ያረገዘች ሴት ዒዳ የምትቆጥር ብትሆን ዒዳዋን የምታጠናቅቀው ሁለተኛው ልጅ ሲወለድ ነው። ኢብኑ ዑሰይሚን

- በምትወልድበት ጊዜ ምንም አይነት ደም ያላጋጠማት ሴት መታጠብ ግዴታ አይሆንባትም። ምክንያቱም ደም ካልፈሰሳት ኒፋስ ላይ አይደለችምና። በርግጥ ይሄ አይነት ክስተት አያጋጥምም። ካጋጠመም እጅግ በጣም ጥቂት ሴቶች ላይ ብቻ የተገደበ ነው።

ዉርጃና ኒፋስ

- ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩም ይሁን በሰው ሰራሽ ምክንያት አራት ወር የሞላውን (ነፍስ የተዘራበትን) ጽንስ ያስወረደች ሴት የሚፈሳት ደም የኒፋስ ደም ተደርጎ እንደሚወሰድ ሁሉም ዑለማኦች ተስማምተዋል፡፡

- አራት ወር ባይሞላውም ያስወረደችው ጽንስ የሰው ቅርጽ (እጅ፣ እግር፣ጭንቅላት…) ከተፈጠረለት በኋላ (81 ቀን) ያለፈው ከሆነም የኒፋስ ደም ተደርጎ መወሰዱ ትክክለኛው አቋም እንደሆነ አብዛኛዎቹ ምሁራኖች ጠቅሰዋል።

- ያስወረደችው ምንም አይነት የሰውነት ቅርጽ የሌለው ከሆነ ለምሳሌ የረጋ ደም ወይም የተበጣጠሰ ስጋ ብቻ ከሆነ ግን ይሄን ተከትሎ የሚፈሰው ደም የኒፋስ ብይን አይሰጠውም፡፡ እንደ በሽታ ደም ነው የሚታየው፡፡ ምንነቱ ባልታወቀ ነገር ሶላት፣ ጾምና መሰል ሸሪዓዊ ጉዳዮች አይተውም ይላሉ።

ኒፋስ ላይ ላለች ሴት የተፈቀዱና የተከለከሉ ጉዳዮች

- ሀይድ ላይ ላለች ሴት የተፈቀዱ ጉዳዮች በሙሉ ኒፋስ ላይ ላለች ሴትም ይፈቀዱላታል። ሀይድ ላይ ላለች ሴት ያልተፈቀዱ ጉዳዮች ሁሉ ኒፋስ ላይ ላለች ሴትም አይፈቀዱላትም። መረጃውም ነብዩ ሀይድና ኒፋስ ልዩነት እንደሌላቸው በሚገልጽ መንገድ ሀይድን ኒፋስ ብለው መጥራታቸው ነው። ኢማሙ ሸውካኒ፣ ኢብኑ ቀዳማህ፣ ነወዊይ እና ኢብኑ ረጀብ በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም ምሁራኖች መስማማታቸውን ገልጸዋል።

- في الصحيحين أن عائشة أم المؤمنين رضي الله عنها كانت قد أهلت بالحج مع رسول الله، فدخل عليها وهي تبكي، فقال: ما يبكيك! أنفست؟
- قال ابن قدامة في المغني: وحكم النفساء حكم الحائض في جميع ما يحرم عليها ويسقط عنها ، لا نعلم في ذالك خلاف"

በሀይድና በኒፋስ መካከል ያለው ልዩነት

- ሀይድ ከዒዳ ዉስጥ ይቆጠራል። ኒፋስ ግን ከዒዳ አይታሰብም። ይህም ማለት ለምሳሌ አንዲት የተፈታች ሴት ልጅ እንደወለደች ወዲያዉኑ ዒዳዋ ይጠናቀቃል። ከወለደች ከደቂቃዎች በኋላ ከሌላ ሰው ጋር ኒካህ ማድረግ ትችላለች። የኒፋሷን ጊዜ እስከምታጠናቅቅ ድረስ ዒዳዋ አይዘገይም ማለት ነው። ዒዳዋን በሀይድ የምትቆጥር ሴት ግን ዒዳዋ የሚጠናቀቀው የሶስተኛው ዙር ሀይድ ሲጀምራት ሳይሆን የሶስተኛውን ዙር የሀይድ ጊዜ ስታጠናቅቅ ነው። ስለዚህ የሀይድ ጊዜ ከዒዳ ዉስጥ ይካተታል ማለት ነው።

- ሀይድ የአቅመ ሄዋንነት መለያ ተደርጎ ይወሰዳል። ኒፋስ ግን ለዚህ አያገለግልም።

- ሀይድ ላይ ያለችን ሴት መፍታት ሀራምነቱ ግልጽ ነው። ንፋስ ላይ ያለችን ሴት መፍታትን በተመለከተ ግን ሀነፊያዎች ይቻላል ይላሉ። ሸይኽ ዑሰይሚኒም ኒፋስ ላይ ያለችን ሴት መፍታትን የሚከለክል መረጃ ስለሌለ ይቻላል የሚል ሀሳብ አላቸው። ነብዩ ሀይድን በኒፋስ መሰየማቸው በትክክለኛ ሀዲስ ስለተረጋገጠ ኒፋስ ላይ ያለችን ሴት መፍታት አይቻልም የሚለው የበለጠ አሳማኝ ነው። ሚስትን መፍታት የሚቻለው ወይ ንጹህ በምትሆንበት ጊዜ ወይም እርግዝናዋ ሲረጋገጥ መሆኑንም የሚገልጹ ጥቅል ሀዲሶች

ኒፋስ ላይ ያለችን ሴት መፍታት ሀይድ ላይ ያለችን ሴት ከመፍታት እንደማይለይ ያሳያሉ። ስለዚህ ኒፋስ ላይ ያለችን ሴት መፍታት ሀይድ ላይ ያለችን ሴት ከመፍታት ተለይቶ አይታይም፡፡

የኒፋስ ደም ማቆሙን ማረጋገጫ መንገዶች

- ሀይድ ላይ ያለች ሴት የሀይድን ማቆም የምታረጋግጥባቸው ዘዴዎች ሁሉ የኒፋስ ደም ማቆም አለማቆሙን ማረጋገጫ መንገዶች ናቸው፡፡ እነሱም የነጭ ፈሳሽ መፍሰስ፣ ጥጥናመሰል ልብሶችንበመጠቀም ደሙ ሙሉ በሙሉ ማቆሙን ማረጋገጥ እንድሁም አንድቀን ከነሌሊቱ ምንም አይነት ፈሳሽ አለማየት ናቸው፡፡

የሀይድና ኒፋስ አስተጣጠብ

- የመታጠብ ግዴታነት የሚጸናው በደም ፍሰት ነው። ደም ያላጋጠማት ሴት እንዲትታጠብ አትገደድም። ትጥበቱ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ደግሞ የደሙ ማቆም ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ ይወሰዳል። ደሙ ሳይቆም የታጠበች ሴት አልነጻችም ማለት ነው።

- ከሀይድ ወይም ከኒፋስ ደም ለመጽዳት መታጠብ ራሱን የቻለ አምልኮት ነው፡፡ ስለሆነም ኒይያ ያስፈልገዋል፡፡ ከሀይድ መንጻትን ሳታስብ ብትታጠብ ከሀይድ እንደጸዳች አይቆጠርላትም።

◆ عن عمر رضي الله عنه انه سمع رسول الله يقول "إنما الأعمال بالنيات وإنما لكل إمرء مانوى " متفق عليه

- ሀይድ ወይም ኒፋስ ላይ ያለች ሴት መላ አካሏን የመታጠብ ግዴታ አለባት፡፡ ምንም አይነት ዉጫዊ የሰውነት ክፍል አይታለፍም፡፡

- አንድት ሴት ጁኑብን በምትታጠብበት ወቅት ጸጉሯን መፍታት አይጠበቅባትም፡፡ ለሀይድና ለኒፋስ ትጥበት ግን ጸጉሯን በመፍታት ማዳረስ ግድ ይላታል ይላሉ ጥቂት ምሁራኖች፡፡ በትክክለኛ ሃዲሶች ጸጉሯን በጣም አድርጋ እንድታሸውና ራሷን

በሙሉ እንድታዳርስ ተነግሯል። በዚህ ላይ ተመስርተው አብዛኛዎቹ ምሁራኖች ጸጉርን መፍታት የሚወደድ ተግባር እንጅ ግዴታ እንዳልሆነ ያምናሉ። የተሻለውም አቋም ይህ ነው። ምክንያቱም የሀይድ እና የጁኑብ ትጥበት ሁለቱም በትጥበት ደረጃ የሚያለያያቸው ትልቅ ነጥብ የለም። በትጥበቱ ዙሪያ የተቀመጠው ወሳኝ ቁምነገር ራሷ (ጭንቅላቷ) ሙሉ በሙሉ በዉሀ እንድዳረስ መሆኑ ግልጽ ነው። ለጥንቃቄ ሲባል ግን ጸጉሯንም ሁሉ ማዳረስ ተገቢ ነው።

- عن أسماء انها سألت النبي صلى الله عليه وسلم عن غسل المحيض فقال... ثم تصب على رأسها فتدلكه دلكا شديدا حتى تبلغ شؤون رأسها ثم تصب عليه الماء .... رواه مسلم
- عن عائشة قالت : كنا نغتسل وعلينا الضماد ، ونحن مع رسول الله محلات ومحرمات. رواه ابو داود
- قال إبن عبد البر في التمهيد والشافعي في الأم : وغسلها من الحيض كغسلها من الجنابة لا يختلفان"

- ሀይድን ወይም ኒፋስን ለማስወገድ በማሰብ መላ ሰውነቷን ራሷንም ጭምር በዉሃ ያዳረሰች ሴት ከሀይድ ወይም ከኒፋስ ነጽታለች። ይህ ግዴታ የሆነው አስተጣጠብ ነው።

- ሱንናዊዉ አስተጣጠብ ግን መጀመሪያ ኢስቲንጃእ ታደርጋለች። ከዚያም በሳሙና ወይም በሌላ ነገር እጆቿን

ታጸዳለች። ከዚያም ሀይድን ለማስወገድ በመነየት ዉዱእ ታደርጋለች። እግሮቿን ከፈለገች መጨረሻ ላይ ከፈለገች ደግሞ ዉዱእ በምታደርግበት ጊዜ መታጠብ ትችላለች። ዉዱእ ስታደርግ ያጠበቻቸውን የሰውነት ክፍሎች ቀሪ አካሏን ስትታጠብ ዳግም መታጠብ አይጠበቅባትም። ከዚያም በጸጉሯ ላይ ሶስት ጊዜ ሶስት እፍኝ ዉሃን እያፈሰሰች በደንብ ታሸዋለች። ራሷ በደንብ ሲረጥብ ተጨማሪ ዉሃ በማፍሰስ መላ ራሷን ታዳርሳለች። መጀመሪያ ቀኝ የራስ ክፍሏን ቀጥላም ግራውን ክፍል በማስከተልም መሀል ክፍሉን መታጠቧም ሱንና ነው። ራሷን አዳርሳ ከታጠበች በኋላ ቀኝ የገላዋን ክፍል ትታጠባለች። ቀሪውን የግራ ጎኗን አስከትላ ከታጠበች በኋላ መጨረሻ ላይ ሚስክ የተደረገበት ጥጥ ወይም ሽቶ የተደረገበትን ፎጣ በመጠቀም ደም የሚያገኘውን አካሏን በማደራረቅ ታጠናቅቃለች።

- ሰውነቷን ከመታጠቧ በፊት ዉዱእ አደረገችም አላደረገችም ሀይድን ወይም ኒፋስን ለማስወገድ አስባ እስከታጠበች ድረስ ኋላ ላይ ዉዱእ ማድረግ አይጠበቅባትም። ትልቁን ሀደስ ለማስወገድ የሚደረገው ኒይያ ትንሹን ሀደስም ያካተተ ነው። ስለዚህ ዉዱእም እንዳደረገች ነው የሚቆጠረው ማለት ነው። ነብዩም ሰውነታቸውን ከታጠቡ በኋላ ዉዱእ ማድረጋቸውን

የሚጠቁም አንድም መረጃ የለም። ይህም የማሊኪያዎች፣ የሻፍዒያዎችና የሀነፊያዎች ምርጫ ነው።

◆ قال النبي للرجل بعدما أعطاه الماء ليغتسل به من الجنابة : خذ هذا فأفرغه عليك" رواه البخاري

◆ قال ابن عبد البر: الله عز وجل إنما فرض على الجنب الغسل دون الوضوء ... وهذا إجماع لا خلاف فيه بين العلماء"

● የሀይድና ኒፋስ ትጥበት ግዴታነቱ ወዲያዉኑ ደሙ እንዳቆመ የሚጸና አይደለም። ሀይዷ ወይም ኒፋሷ ሙሉ በሙሉ ማቆሙን እንዳረጋገጠች ባስቸኳይ የምትፈጽመው ግዴታ የሆነ ተግባር ካለ ግን ቶሎ መታጠብ ግዴታ ይሆንባታል። ለምሳሌ ከሀይድ የነጻችው ጸሀይ ልትጠልቅ አካባቢ ከሆነ ዐስርን መስገዷ ግዴታ ስለሆነ ወዲያዉኑ መታጠብ ግዴታ ይሆንባታል። ነገር ግን ሀይዷ ያቆመው ዐስር እንደገባ ከሆነ ሰፊ ጊዜ ስላላት ዘግየት አድርጋ መታጠብ ትችላለች። ወዲያውኑ መታጠቡ የሚወደድ ተግባር መሆኑ ግን መዘንጋት የለበትም።

● የሀይድና የኒፋስ ደም ነጃሳ ነው።

◆ قال الله عز وجل { وَيَسْأَلُونَكَ عَنِ الْمَحِيضِ قُلْ هُوَ أَذًى} البقرة -٢٢٢

◆ ولقول النبي لفاطمة بنت ابي حبيش ... فاغسلي عنك الدم ... روه البخاري

◆ قال الشوكاني : واعلم ان دم الحيض نجس بإجماع المسلمين " نيل الأوطار ١/٥٧

ስለሆነም ይህ ደም የነካውን ልብስ ማጠብ ግድ ይላል፡፡ ለማጠብም ሳሙናና መሰል ማጽጃዎችን መጠቀም ይበረታታል፡፡ ሳሙናና መሰል ማጽጃዎችን ለመጠቀም አቅም የሌላት ከሆነ በዉሃ ብቻ ማጠብ ይኖርበታል፡፡ በዉሃ ካጠበችው በኋላ በልብሱ ላይ የደሙ ተጽእኖ ቢቀር በነጃሳነት አይወሰድም፡፡ የደሙ አሻራ አይጎዳም ተብሏል፡፡

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لخولة بنت يسار: يَكفيكِ غسلُ الدَّمِ ولا يضرُّكِ أثرُهُ . رواه أبوا داود وصححه الألباني

● ከሀይድም ይሁን ከኒፋስ ለመንጻት ዉሃ መጠቀም እስከተቻለ ድረስ ከዉሃ ዉጭ ያሉ መጸዳጃዎችን መጠቀም አይቻልም፡፡ ሀዲሱም ይሄንኑ ያስረዳል፡፡

◆ قال النبي صلى الله عليه وسلم لخولة بنت يسار: يَكفيكِ الماء ... . رواه أحمد وصححه أحمد شاكر

● የሀይድ ደም ማቆሙን ካረጋገጠች በኋላ ሰውነቷን ለመታጠብ ዉሀ ያላገኘች ወይም ዉሃው ቢገኝም መጠቀም ያልቻለች ሴት ተየሙም ታደርጋለች፡፡ ከዚያም የጸዳች ሴት የምታደርጋቸውን ማንኛውም ተግባራቶች መፈጸም ይኖርባታል፡፡

◆ {فلم تجدوا ماء فتيمموا صعيدا طيبا} النساء -٤٣

ተጠናቀቀ

ማጣቀሻዎች

1) شرح الممتع على زاد المستقنع ---------------- محمد بن صالح العثيمين

2) أحكام الطهارة جزء ٨ & ٩ ---------------------- دبيان محمد الدبيان

3) أحكام النساء للألباني ---------------- محمد بن حامد بن عبد الوهاب

4) تمام المنة في فقه الكتاب وصحيح السنة ----- عادل بن يسوف العزازي

5) صحيح فقه السنة -------------------------------- كمال سيد سالم

6) الثمر المستطاب في فقه السنة والكتاب ------ محمد ناصر الدين الألباني

7) موقع شيخ عبد العزيز بن باز

8) موقع درر السنية ------------ بإشراف علوي بن عبد الرحمن السقاف

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

መግቢያ---1

የሀይድ ትርጉምና ጥቅል መልእክቶች--------------------------4

የሀይድ ደም መለያዎች--8

ሀይድ እና እድሜ---9

ሀይድና የጊዜ ቆይታው---11

ልምድን ያልጠበቀ ሀይድ ---------------------------------------17

ሀይድ ላይ ላለች ሴት የተፈቀዱ ጉዳዮች-----------------------20

ሀይድ ላይ ላለች ሴት የተከለከሉ ጉዳዮች----------------------22

የሀይድ ማዘግያ እና ማፍጠኛ መድሃኒቶችን መጠቀም---------44

የሀይድ ማቆም ማረጋገጫ መንገዶች---------------------------45

ኢስቲሀዷ (የበሽታ ደም)---------------------------------------47

ኢስቲሀዷ ላይ ያለች ሴት ምን ይጠበቅባታል?-----------------51

ኢስቲሀዷ ላይ ያለች ሴት ሶላት አሰጋገድ-----------------------52

ኒፋስ (የውልደት ደም)--56

የኒፋስና የጊዜ ትስስር--56

ዉርጃና ኒፋስ ---59

ኒፋስ ላይ ላለች ሴት የተፈቀዱና የተከለከሉ ጉዳዮች-----------60

በሀይድና በኒፋስ መካከል ያለው ልዩነት-----------------------61

የኒፋስ ደም ማቆም ማረጋገጫ መንገዶች---------------------62

የሀይድና የኒፋስ አስተጣጠብ----------------------------------63

ማጣቀሻዎች---68

ሰዎችን ወደ መልካም ነገር መጠቆም የሚያስገኘውን አጅር በማሰብ ይች አጭር ማስታወሻ ለብዙዎች ትደርስ ዘንድ የቻሉትን ያክል ያሰራጩት።

ለአስተያየትዎ nahmed.siraj@gmail.com *ወይም*

http://t.me/Nasir_Ah ይጠቀሙ።

الحمد لله الذي بنعمته تتم الصالحات وصلى
الله وسلم وبارك على محمد وعلى اله
وصحبه ومن اهتدى بهديه إلى يوم الدين.